# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 197 መጋቢት 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# «የጉራጌ ሕዝብ ችግሮችን በውይይት የሚፈታ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የጉራጌ ሕዝብ የሚነሡ ችግሮችን ገንቢ በሆነ ተሳትፎና ውይይት የሚፈታ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትናንት ከጉራጌ ዞን የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በወልቂጤ ከተማ ተወያይተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው እንደገለጹት፣ የጉራጌ ሕዝብ ችግሮችን ገንቢ በሆነ ተሳትፎና ውይይት የሚፈታ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው። ዛሬ ባደረግናቸው ውይይቶች ያነሷቸውን ሥጋቶችና ተስፋዎች በመስማቴ ደስተኛ ነኝ ብለዋል። መንግሥት በየደረጃው ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚሠራም ገልጸዋል።

መለያየትን ከማባባስ ይልቅ፣ በውይይት በሕዝቡ ውስጥ ያለውን ትልቅ ዐቅም በመጠቀም አንድነትን የበለጠ ለማሳደግ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ መናገራቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች የሰላም፣ የልማትና አስተዳደራዊ ጥያቄዎችን አቅርበዋል። ነዋሪዎቹ በጥያቄዎቻቸው በዞኑ የውሃ፣ የመንገድ፣ የጤናና የትምህርት ተቋማት ተደራሽነት ችግር መኖሩን ተናግረዋል። ይህም በዞኑ ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና መፍጠሩን ገልጸዋል። የጉራጌ ዞን ራሱን ችሎ በክልልነት በመደራጀት የልማት ጥያቄዎቹን ለመፍታት ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል የሚል ጥያቄ ተነስቷል። የክልልነት ጥያቄን እንደሸፋን በመውሰድ በዞኑ አብረው በጋራ የኖሩ ሕዝቦችን ለማጋጨት የሚሠሩ አካላት መኖራቸውን


"የጉራጌ ሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ

ቪክቶሪያ ክዋክዋ

## በግጭት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት በሚደረገው እንቅስቃሴ የዓለም ባንክ ድጋፍ ያደርጋል


ገጽ 4


# በአማራ ክልል የ67 ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ እየተካሄደ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው የ67 ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ::

የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ወንድወሰን አቢ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል በጦርነቱ ጉዳት ከደረሰባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርት ሚኒስቴር የ45 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በ720 ሚሊዮን ብር የመልሶ ግንባታ ሥራ እያካሄደ ነው:: ክልሉ ደግሞ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች መልሶ ግንባታ ፈንድ ጽሕፈት ቤት በተገኘ የ332 ሚሊዮን ብር 22 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ እያከናወነ ነው::


በአማራ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ኢጋድ የኢትዮጵያ መንግሥት ድርቅን ለመቋቋም የሚያደርገውን ጥረት ይደግፋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት እንደሚደግፍ የምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) አስታወቀ:: ኢጋድ በኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ከአራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል::


ኢጋድ የኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ





AMG STEEL FACTORY
ኤ.ኤም.ጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
Our Products
GI-Coil Color Coil Tiles
Ega Sky Tiles Corrugated Sheet Curving Ridge Sky Ridge V-Gutter Accessories
Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80/ 0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

AfriSky PLC ETHIOPIA
Our Products
Billet RHS Wire Rod Re-bar CZU H-BEAM Nail Streel Structure Tanker
Akaki, Gelan
0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06



አቶ ጊደና መድህን

# የሕወሓት ከሽብርተኝነት መዝገብ መሰረዝ ሰላምን ለማጽናት አጋዥ ነው

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት ከሽብርተኛ መዝገብ መሰረዙ የትግራይ ሕዝብ ችግርን ለማቃለልና ሰላምን ለማጽናት ይረዳል ሲሉ የትንሳኤ 70 እንደርታ ፓርቲ (ትሰፓእ) አስተባባሪ አቶ ጊደና መድህን ገለጹ፡፡

አቶ ጊደና ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ አጠቃላይ የሰሜኑ ክፍል ሰላም ከማጣቱ የተነሳ የሰላም ትሩፋት የምንላቸው ነገሮች በእጅጉ መጥፋታቸውን ገልጸው፤ ሕወሓት ከሽብርተኛ መዝገብ መሰረዙ የትግራይ ሕዝብ ችግርን ለማቃለል ይረዳል ብለዋል፡፡

በተለይ የትግራይ ሕፃናት ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ፤ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲሠሩ እና ገበሬው እንዲያመርት ዕድል እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ ይህ የሕዝቡን ችግር ለማቃለል እንደሚረዳ አብራርተዋል፡፡

የፌዴራል መንግሥት እና ሕወሓት ያደረጉት የሰላም ስምምነትና አሁን ደግሞ ፓርቲው ከሽብርተኝነት እንዲነሳ መደረጉ ሕዝቡን ወደ ተሻለ መንገድ ከማስገባቱም ባሻገር እንደ አገር ሰላምን ለማጽናት አጋዥ ነው ብለዋል፡፡

በነበረው የሰላም እጦት ምክንያት አጠቃላይ የትግራይ ሕዝብ በተለይ መንግሥት ሠራተኛው ለ19 ወራት ደመወዝ ሳይከፈለው በአስከፊ ችግር ውስጥ ከመቆየቱ አንፃር የሕወሓት ከአሸባሪነት መዝገብ መሰረዝ የሕዝቡን ችግር ሊያቃልል የሚችል መሆኑንም አንስተዋል፡፡

እንደ አቶ ጊደና ገለፃ፤ የሕወሓት ከሽብርተኝነት መዝገብ መነሳት የጦርነቱ አየር የፈጠረው ጋሬጣና ከባድ ስሜት እንዲወገድ እንዲሁም መልሶ ግንባታው እንዲፋጠን ዕድል የሚፈጥር ነው፡፡ ማንኛውም አደረጃጀትም ይሁን ግለሰብ በሕጋዊ መንገድ ተንቀሳቅሶ ለአገር እድገት የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ በጋራ የመሥራት ባህልን ማዳበር አለበት ብለዋል፡፡

‹‹የትግራይ መዳከም ለማንም አይበጅም›› ያሉት አቶ ጊደና፤ ትግራይ እንድትጠነክርና ሕዝቡ ተረጋግቶ እንዲኖር እንዲሁም ምርታማ ገበሬ እና በዕውቀት የበለፀገ ወጣት እንዲበራከት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

በተለይ የተበላሸው የፖለቲካ አካሄድና የተጎሳቆለው ኢኮኖሚ እንዲታከም በውጭ አገር ይሁን በአገር ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ሰዎችና ፖለቲከኞች እንዲሁም የሚዲያ አካላት ጠቃሚ የሆነ ሃሳብ በማበርከት ትግራይን መልሶ በማልማት እና በመደገፍ ሊረባረቡ ይገባል ብለዋል፡፡

# ጮቄ ኢኮ ቱሪዝም ሽልማት የአገርን ገጽታ ለመገንባት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ተገለጸ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከዓለም የቱሪዝም ድርጅት በቅርቡ የተቀበለችው የጮቄ ኢኮ ቱሪዝም ሽልማት የአገርን ገጽታ ከመገንባትና ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አኳያ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሽልማቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለሆነ ብዙ እውቅና ለማግኘት በተለይም ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ የልማት ትኩረትን ለማግኘት ትልቅ ዕድል ይፈጥራል፡፡

በተጨማሪም ልዩ ልዩ ኢንቨስትመንቶች ወደ ቦታው የመሄድና በአካባቢው አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ- ልማቶች እንዲሁም ቱሪዝሙን የሚደግፉ ተጨማሪ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ዕድል ያመቻቻል፡፡

ጮቄ ኢኮ ቪሌጅ ተብለው በዓለም ከሚጠሩ ስፍራዎች መካከል በቀዳሚነት መመረጡ ለአገር ገጽታ ግንባታ ሚናው ጉልህ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ቱሪስቶች እውቅና ላገኙ ቦታዎች ቅድሚያ ስለሚሰጡ በዓለም የቱሪዝም ድርጅት እውቅና ያገኙትን ቅድሚያ ሰጥተው የመጎብኘት ፍላጎት ይጨምራል ብለዋል፡፡

ሽልማቱ የዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ድርጅቶች ድጋፍ ለማድረግም ሆነ በቦታው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ዕድል የሚፈጥር ነው፤ እንዲሁም ለአካባቢው ማኅበረሰብ ተጨማሪ ኢኮኖሚውን የሚደግፍለት የቱሪዝም የገበያ ዕድል ያገኛል፡፡

አቶ ስለሺ አክለውም የጮቄ በኢኮ ቪሌጅነት መመረጥ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት እና የማኅበረሰቡን ባህል፣ ወግ ልማድና የአኗኗር ዘዬ ትኩረት ሰጥታ እንደምትጠብቅ ማሳያ ነው፡፡

ጮቄ በዓለም ምርጥ የቱሪዝም መንደር ተብሎ መመረጥ -የቦታው ማራኪነት፣ አካባቢው ላይ ያለው የተፈጥሮ ሀብት፣ በአካባቢው ያለው ማኅበረሰብ የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የእንግዳ አቀባበል ሥርዓት እንደትልቅ ግብዓት ሆኖታል፡፡

ቦታውን ይበልጥ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን ከመሳብ አኳያ በትኩረት እየሠራን ነው ያሉት አቶ ስለሺ፤ የአካባቢውን ሥነምህዳር የማይጎዳና በጥብቅ ደኑ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ እንስሳትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ አገልግሎቶች ማሟላት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በሚኒስቴሩ አስቸኳይ ኢንቨስትመንት ያስፈልጋቸዋል ተብለው ከተለዩ የቱሪስት መንደሮች መካከል አንዱ ጮቄ ተራራ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

የምሥራቅ ጎጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ወ/ሮ ውዱዓለም አልማው በበኩላቸው፤ ጮቄ በዓለም ምርጥ የቱሪዝም መንደር ሆኖ መመረጡና ከዓለም የቱሪዝም ድርጅት ሽልማት መቀበሉ ለዞኑ የቱሪዝም መነቃቃት ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

ባለፉት ጊዜያት ጮቄ ምርጥ የዓለም የቱሪዝም መንደር ተብሎ ከተመረጠ በኋላ የቱሪስት ፍሰቱ ጨምሯል ያሉት ኃላፊው፤ በርካታ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት የማልማት ፍላጎት እንዳላቸው አሳይተዋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ቦታው ዓለም አቀፍ እውቅና ማግኘቱ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ተጨማሪ የሥራ ዕድል የሚያገኝበት ዕድል እንዲሁም ከቱሪዝሙ ጎን ለጎን ኢኮኖሚውን የሚደግፍበትና የአካባቢውን ሙሉ ገጽታ የሚያስተዋውቅበት ሰፊ ዕድል ፈጥሮለታል ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ውዱዓለም ገለጻ የቱሪስት ፍሰቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ይበልጥ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግና ወደ ስፍራው የመጣው ቱሪስት ሙሉ አገልግሎት አግኝቶ እንዲመለስ ለማድረግ በትኩረት እየሠራን ነው ብለዋል፡፡



# በጋምቤላ ክልል ለመጀመሪያ ጊዜ ከበጋ መስኖ ከአራት ሺ በላይ ኩንታል የስንዴ ምርት ይጠበቃል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከአራት ሺ 170 በላይ ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅ የጋምቤላ ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የጋምቤላ ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አጃ ኩቸላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በበጋ ስንዴ 480 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሄክታር ማልማት ተችሏል። ከዚህም አራት ሺ 170 ኩንታል የስንዴ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል።

በክልሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚተገበረው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በሙከራ ደረጃ 139 ሺ ሄክታር መሬት በአራት የጋምቤላ ክልል ወረዳዎች ላይ በትኩረት እየሠራን ነው። ለዚህም ከአንድ ሄክታር 30 ኩንታል ስንዴ በማምረት በአጠቃላይ አራት ሺህ 170 ኩንታል ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል። ኃላፊው በበጋ ስንዴ ዘር ጊዜ በክልሉ በነበረው ከፍተኛ ዝናብ ሁኔታ እና ከፍተኛ ሙቀት ጋር ተያይዞ በወቅቱ ወደ ሥራ ለመግባት አመቺ ስላልነበረ የታቀደውን ያህል መሬት በስንዴ መሸፈን አልተቻለም ብለዋል።

የበጋ ስንዴ ልማት ሥራን በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች ለማካሄድ የፌዴራል መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ሚኒስቴር ለክልሉ 36 ትራክተሮችና 150 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በድጋፍ መልክ መስጠቱን አስታውሰው፤ በዚህም በክልሉ ለሚገኙ 14 ወረዳዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ትራክተሮች እንዲያገኙ መደረጉን ነው የተናገሩት።

በተጨማሪም የግብርና ሚኒስቴር ከፌዴራል ግብርና ምርምር ጋር በጋራ በመሆን የማዳበሪያ አቅርቦትና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መስጠታቸውን አብራርተዋል። እንደ አቶ አጃ ገለጻ፤ በበጋ ስንዴ ልማት ሥራ ከአራት ሺ በላይ ገበሬዎች የተሳተፉበት ሲሆን ከአንድ ሺ 400 በላይ ሰዎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

የበጋ መስኖ ስንዴ በደጋማ አካባቢ የሚበቅል እንጂ ጋምቤላ ላይ መብቀል እንደማይችል መላምቶች የነበሩ ቢሆንም በ2015 ዓ.ም በሰፊው ትኩረት በመስጠት ወደ ሥራ በመግባታችን አበረታች ውጤት እያየንበት ነው። ይህም በክልሉ ብሎም በአገር ላይ ያለውን የኑሮ ውድነት ከማረጋጋት፣ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ እንደአገር የተጀመረውን የስንዴን ምርት በአገር ውስጥ ምርት ከመተካት እና ለውጭ ገበያ ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው ሲሉ ተናግረዋል።

በክልሉ ያለው አየር ሁኔታ፣ በቂ የመስኖ መሠረተ ልማት አለመኖር፣ የሕዝብ ተሳትፎና ተነሳሽነት ውስን መሆን ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ እንደተግዳሮት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ገልጸው፤ ለቀጣይ የበጋ መስኖ ሥራ ከዚህ የበለጠ ምርት ለመሰብሰብ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋቱ ሂደት ሸማቹ ማኅበረሰብ የራሱን ድርሻ ይወጣ!

የኑሮ ውድነት በዓለምአቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን መሰረታዊ ችግር ሆኖ ቀጥሏል። የገበያን ዋጋ ለማረጋጋት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም የኑሮ ውድነቱ በሚፈለገው ደረጃ አልወረደም፡፡ በኮንስትራክሽኑ ዘርፍ የሚታየው የማቴሪያል ዋጋ በተለይ የሲሚንቶ ዋጋ መጠነኛ የዋጋ መቀነስ አሳይቶና ገበያው ተረጋግቶ የቆየው ለትንሽ ጊዜ ብቻ ነው። አሁን ግን የሲሚንቶ ዋጋ በኩንታል እስከ 1950 ብር እየተሸጠ ይገኛል። የእህል ዋጋን ለማረጋጋት በመንግስት ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም ወደሚፈለገው ደረጃ ሊደርስ አልቻለም፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም መንግስት ገበያን ለማረጋገት እየሰራ ነው።

በሸማቾች አማካይነት ገበያን ለማረጋጋት መንግስት የወሰደው እርምጃ በተለይ ጤፍ ባለበት ዋጋ ላይ እንዲቆም አድርጎታል። የኢኮኖሚ ገቢው አነስተኛ የሆነው ኅብረተሰብ በነጋዴዎች ከመበዝበዝ ይልቅ ከሸማቾች ማኅበራት እህል በመገብየት የዕለት ኑሮውን እንዲደጉም አስችሎታል ። ሆኖም ይሄ በቂ አልሆነም።

ከንግድ ሥርዓቱ አለመስተካከል በተጨማሪ የኑሮ ውድነትን ከሚያባብሱ ምክንያቶች ሌላኛዎቹ የንግዱ ማህበረሰብ" ነገ ከፍተኛ ዋጋ ያወጣል" በሚል የሚያደርገው መደበቅ፣ በሌላም በኩል ደግሞ ሸማቹ ማኅበረሰብ ምርት ከገበያ ላይ ሊጠፋ ይችላል ብሎ በመስጋት በብዛት ገዝቶ ለማከማቸት የሚያደርገው መስገብገብ ጭምር ነው። ለኑሮው መወደድ ሌሎች ዓለምአቀፋዊና አገራዊ ምክንያቶች ቢኖሩም እንኳን ያንን ምክንያት የሚያባብሰው ነጋዴውና ሸማቹ ጭምር ነው።

የንግዱ ማኅበረሰብ ህገወጥ ወይም ሰው ሰራሽ የኑሮ ውድነት እንዲፈጠር ሲያደርግ ሸማቹ ማህበረሰብ "በህገ አምላክ" ብሎ ከሚመለከተቻው አካለት ጋር በመሆን ሕገወጦች ስርዓት እንዲይዙ ማገዝና በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ማድረግ አለበት። በእኛ አገር ግን መብቱን የሚጠይቅ ሸማች አለ ብሎ ደፍሮ መናገር አይቻልም። ለገዛው ማንኛውም ምርት ደረሰኝ መጠየቅና መቀበል መብቱ ቢሆንም ይሄንን ሲተገብር አይታይም። የሸማቾች ማኅበራት ለሸማቹ የሸቀጣ ሸቀጥና የእህል አቅርቦት ከመሆን በተጨማሪ የሸማቹ መብት የሚከበርባቸው አውዶች እንዲሆኑ መስራት ያስፈልጋል።

ስለሆነም ሸማቹ ማኅበረሰብ በግብይት ወቅት የሚፈጸሙ የንግድ ጥሰቶችን መከላከል እንዲችልና ለመብቱ እንዲታገል ግንዛቤውን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዙሪያ መስራት የሚገባቸው የሸማቹ መብት ተከራካሪና ተቆርቋሪ አካላትና ማህበራት ሊኖሩና ሊጠናከሩ ይገባል።

"በደረሰኝ ግብይት ይፈጽሙ መብትዎን ያስከብሩ" በሚል መሪ ሃሳብ ሰሞኑን የሸማቾች መብት ቀን ታስቦ ውሏል። በግብይት ወቅት የሚደርሱ የመብት ጥሰቶችን በሕግ አግባብ ብቻ መፍታት ስለማይቻል ሸማቹ መብቱን እንዲያስከብር ግንዛቤ ለመፍጠር የተካሄደ ነበር።

በተቋማት በኩል የንግድ ሥራ ጥሰቶች ሲፈጸሙ በሕግ አግባብ ማስተካከያ ርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣ የግብይት ሂደቶችንና የዋጋ ጭማሪዎችን ለመከላከል ለመብቱ የሚታገልና ጠያቂ ሸማች ማኅበረሰብ መፍጠር አስፈላጊ ነው ፡፡

ሸማቹ መብቱን አውቆ ሲገዛ የማማረጥ፤ ካልሆነውም የመተው መብቱ በተጨማሪ በግብይቱ ጉዳቶች ሲደርስበት ካሳ የመጠየቅ መብት እንዳለው ሊያውቅ ይገባል።

በግብይት ሂደት ውስጥ ሸማቹ ጥራቱን የጠበቀና፣ ጊዜው ያላለፈበት ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ የመግዛትና ከመረጠው የንግድ ተቋም የሚፈልገውን ምርት የመሸመት መብትም አለው።

ሸማቹ ለግብይት ሲወጣ መብቱን የማይጠቀም ከሆነ ደግሞ ነጋዴው እንደፈለገው የዋጋ ጭማሪ ሊያደርግ ስለሚችል ይህንን መታገል ያስፈልጋል። ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቱን ጠንቅቆ ባለማወቁ የተነሳ የሕግ መብት ጥሰት ሲከሰት ይስተዋላል። ስለሆነም ሸማቹ ማኅበረሰብ የተቀመጠለትን መብት እንዲገነዘብ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቱን እንዲያውቅና በግብይት ወቅት ክፍተት ሲፈጠር ቅሬታውን ለማቅረብ ወዴት መሄድ እንዳለበት እንዲያውቅና በተሰጠው መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ጥረት ሊደረግ ይገባል። በግብይት ወቅት የሚፈጸሙ የሕግ ጥሰቶችን ለመከላከል ሸማቾች በደረሰኝ ግብይት ተጠቅመው መገበያየት ይኖርባቸዋል ።

ይሄ ልምድ ባለመዳበሩ ግን በአሁኑ ወቅት ደረሰኝ መጠየቅ እንደቁም ነገር አለመቁጠርና የንግዱ ማኅበረሰብም ደረሰኝ ሲጠየቅ የሚያጉረመርምበት ሁኔታ ነው ያለው። ነጋዴውም ለሰጠው ማንኛውም ግብይት ጥያቄ ሳይቀርብለት ደረሰኝ መስጠት ግዴታው መሆኑን ፤ ተጠቃሚውም ትክክለኛው ደረሰኝ ማግኘት መብቱ እንደሆነ መታወቅ አለበት። ይሄ ሲሆን ነው አገር የምታድገውና ህገወጥነት እየቀነሰ ህጋዊነት እያበበ የሚሄደው።

ለዚህ ደግሞ ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል። በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚከበር የሸማቾች ቀን መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ ስለማይችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ኅብረተሰቡን በማስተማር የህግ ስርዓቱን የሚያደነቃቅፉትን ደግሞ በመቅጣትና በማስተማር እንዲሁም ለሌሎች እንዲማሩበት በማድረግ የሸማቹን መብትና ጥቅም እንዲከበር ማድረግ ይገባል። ሸማቹ ማኅበረሰብም መብቱን ለማስከበር ጠንክሮ መስራት አለበት!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ‹‹የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች››

**ፍሬሕይወት አወቀ**

መቼም ይህን አባባል በሰማን ጊዜ ወደ አዕምሯችን ጓዳ ሰተት ብለው የሚመጡት ሁለት ፍጹም የሚመሳሰሉ ነገሮች ስለመሆናቸው የማይካድ ሃቅ ነው። ይሁንና ዛሬ ይህን አባባል ለጽሁፌ ርዕስ ገላጭ ነው ብዬ ስነሳ ታድያ ያለምክንያት አይደለም። ይልቁንም ከሚመሳሰሉ ነገሮች ይልቅ የማይነጣጠሉ ነገሮችን ላሳይበት ስለወደድኩ ነው።

እነዚህ መመሳሰል ሳይሆን ፍጹም መነጣጠል የማይቻላቸው ‹‹የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች›› እንጀራና ኢትዮጵያውያን ናቸው። ኢትዮጵያውያኑ ከእንጀራ ጋር ባላቸው ጥብቅ ቁርኝት የተነሳ ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ ‹‹የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች›› ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ዋናውና ቀዳሚው ምግባችን እንጀራ ነው። የእንጀራው ማባያ ወጥ ምንም ይሁን ምን እንጀራ ለኢትዮጵያውያኑ የየዕለት ምግብ በመሆኑ ምክንያት እንጀራ የማይበላ ኢትዮጵያዊ አለ ማለት አይቻል ይሆናል። ቢባልም ከእውነታ መራቅ አይደለም።

ከዚህ በላይ ግን እንጀራ ለኢትዮጵያውያን ከምግብነቱ ባለፈ የብዙ ነገሮቹ መገላጫ ባህልና እሴቱን ማንጸባረቂያም ጭምር ነው። ለአነብነትም ምርቃት የሚመርቅ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ‹‹እንጀራ ይውጣልህ/ሽ›› ብሎ ነው። ይህ ምርቃት ታድያ በኢትዮጵያ ትልቁ ምርቃት ነው።

ዜጎች ሥራ ፍለጋ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ሲንቀሳቀሱም እንጀራ ፍለጋ ተሰደደ፣ ሄደ፣ ተንገላታ፣ ደከመ ወዘተ... በማለት እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ከእንጀራ ፍለጋ ጋር ይቆራኛል። በተጨማሪም ኢትዮጵያዊ ፈጣሪውን ሲማጸን በጸሎት ውስጥ የዕለት ጉርሱ የሆነውን እንጀራ ሳይነሳ አይቀርም።

ለአብነትም የክርስትና ዕምነት ተከታዮች በጸሎታቸው መካከል ‹‹...የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ...›› የሚል ሐረግ ይጠቀማሉ የሌሎች ዕምነት ተከታዮችም ይህንኑ ሀሳብ የሚጋሩ እንደሆነ ዕምነት አለኝ፡፤

> አፍንጫ ሲነካ አይን ያስቅሳል ለካ‹‹ እንደሚባለው ሆነና ከሰሞኑ የእንጀራ ፈጣሪ በሆነው የጤፍ ምርት ላይ መዲናዋ ስትታመስ ሰነባብታለች

ለኢትዮጵያውያን ከምግብ በላይ ሆኖ ላይ ታች የሚያባዝነው ይህ እንጀራ ታድያ ከዕለት ጉርስ ባለፈ የጓዳችን ሙላት፤ የገጻችን ወዝ በመሆን ከእኛነታችን ነጥለን የማናየው ‹‹የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ›› ዋና ጉዳያችን ነው። እንጀራን እንጀራ ያደረገው ጤፍ ከኢትዮጵያውያኑ መሬት ብቻ መብቀሉም ቁርኝቱን ይበልጥ ሳያጠነክረው አልቀረም። ‹‹አፍንጫ ሲነካ አይን ያለቅሳል ለካ›› እንደሚባለው ሆነና ከሰሞኑ የእንጀራ ፈጣሪ በሆነው የጤፍ ምርት ላይ መዲናዋ ስትታመስ ሰነባብታለች።

ባለፈው ሰሞን ባልተለመደ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ የተስተዋለው የጤፍ ምርት እጥረትና የዋጋ ጭማሪ መነጋገሪያ ሆኖ ሰነባብቷል። ከፍተኛ ጭማሪ ባሳየው የጤፍ ዋጋ ምክንያትም አንድ እንጀራ ከአስር ብር ተነስቶ እስከ 17 እና 20 ብር ድረስ ተሸጧል።

ይህም የኑሮ ውድነቱን አባብሶታል። ‹‹...ደግሞ ባይኔ መጣሽ...›› እንዲል ድምጻዊው ኢትዮጵያዊው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆኖ ከመመሳሰል በላይ ከዕለት ተዕለት ማዕዱ የማይጠፋው እንጀራ ዋጋ በመናሩ የተነሳ የነበረውን ስጋት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲገልጽ እንደነበር ይታወሳል።

እርግጥ ነው የኑሮ ውድነት በየጊዜው አናት አናቱን ለሚለው ሸማች የጤፍ ዋጋ መጨመር አዲስ ነገር አይደለም ይሆናል። ነገር ግን የጤፍ ዋጋ ለማሰብ በሚከብድ መልኩ ድንገት ተነስቶ ሽምጥ መጋለቡና ዋጋው አልቀመስ ማለቱ ሸማቹን ግራ ከማጋባት በላይ መንግሥትም ጉዳዩን ቆም ብሎ እንዲያስብና እንዲያጤን አድርጎታል። መንግሥት ለጉዳዩ በሰጠው ትኩረትም በአሁን ወቅት ያለአግባብ የተሰቀለው የጤፍ ዋጋ እየወረደ መምጣቱን መመልከት ችለናል።

አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከጊዜ ጋር እሽቅድምድም የያዘ የሚመስለው የጤፍ ዋጋ ዕለት ተዕለት እያሻቀበ ሸማቹን ለምሬት ስለዳረገው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኦሮሚያና የአማራ ክልሎች የጋራ መፍትሄ ለማምጣትና ለሰው ሰራሽ እጥረት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ለመፍታት መፍትሄ አምጪ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ጀምረዋል። አገሪቷ የጤፍ ምርትን በገፍ እንዳመረተችና የማምረት ዕምቅ አቅም እንዳላት ስለሚታወቅም ሰው ሰራሽ ሆኑ ችግሮችን መፍታት ከተቻለና የገበያ ስርዓቱ መስመር ከያዘ ለችግሩ ዘለቄታዊ መፍትሄ እንደሚመጣ የሚያጠራጥር አይሆንም።

በከተማዋ የታየው የጤፍ ዋጋ ንረትም በኬላዎች አካባቢ በተፈጠሩ አላስፈላጊና ሕገወጥ ተግባራት ምክንያት እንደሆነ መረጃዎች አመላክተዋል። እርግጥ ነው ሕገወጥ ተግባራት በአገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች እዚህም እዚያም የሚስተዋሉ ቁልፍ ችግሮቻችን ናቸው። እነዚህን ሥር የሰደዱና የገነገኑ ችግሮችን ታድያ በአንድ ጀንበር ነቅሎ መጣል የማይቻል ቢሆንም በጊዜ ሂደት መፍታት እንዲቻል ግን የቤት ሥራውን ከዛሬ መጀመር ያስፈልጋል።

ከኢትዮጵያውያን ገበታ የማይነጠለው ጤፍ ዋጋው በከፍተኛ መጠን በመናሩ ምክንያት ሸማቹ ስጋት ውስጥ ከመግባቱም ባለፈ የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ እንዲሰማውም አድርጓል። ይሁንና በአሁን ወቅት ጤፍን ጨምሮ የምግብ ፍጆታ እቃዎች ገበያን መንግሥት ለማረጋጋት ከላይ ታች እያለ ይገኛል። በመሆኑም መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት አንድ ኪሎ ግራም ጤፍን እንደየደረጃው ከ55 እስከ 68 ብር መሸጥ እንዲችል እየሠሩ መሆኑን እያስረዱ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ በበኩሉም ሰሞኑን በአስደንጋጭ ሁኔታ የናረውን የጤፍ ዋጋን ከረፈደም ቢሆን ገበያውን ለማረጋጋት በአገሪቱ በበቂ ሁኔታ ተመርቷል ያለውን ምርት ወደ መዲናዋ ማስገባት መጀመሩን እየገለጸ ይገኛል። በተለይም በከተማዋ የተፈጠረውን የገበያ ንረት ለማረጋጋት 300 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ምርቶች ለገበያ መቅረባቸው ተገልጿል።

ማንኛውም ችግር የራሱ የሆነ መፍትሔ እንዳለው ሁሉ በገበያው አለመረጋጋትም የተፈጠረውን ችግር ለመቆጣጠር እየተደረገ ያለውን ጥረት ይበል የሚያሰኝና የሚያበረታታ ነው። ይሁንና ‹‹ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ›› የሚለውን የአበው ተረት በአግባቡና በወቅቱ መጠቀም ችግሮችን ከማቅለል ባለፈ ችግሮች የሚፈጠሩበትን ዕድልም የሚያጠብ በመሆኑ ትኩረታችን ዘላቂ መፍትሔዎች ላይ ይሁን። ሰላም!

# በግጭት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት በሚደረገው እንቅስቃሴ የዓለም ባንክ ድጋፍ ያደርጋል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሰሜን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን ግጭት ተከትሎ የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ በሚደረገው እንቅስቃሴ የዓለም ባንክ ድጋፍ እንደሚያደርግ ተገለጸ::

የዓለም ባንክ የምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት ቪክቶሪያ ክዋክዋ በኢትዮጵያ የነበራቸውን ጉብኝት አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፣ የተለያዩ የልማት ጉዳዮች ላይ የጋራ ትብብርን ማጠናከር የሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ከመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ውይይት አድርገናል:: ባንኩ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ጠንካራ አጋርነት በማሳደግ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገትን በዘላቂ ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው:: በተለይም በሰሜን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን ግጭት ተከትሎ የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ በሚደረገው እንቅስቃሴ የዓለም ባንክ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል::

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ተከስቶ በነበረው ግጭት ባንኩ ተልዕኮውን በሚገባ እንዳያከናውን ተግዳሮት ገጥሞት እንደነበር በመግለጽ፤ በፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰው የሠላም ስምምነት በግጭቱ በተጎዱ አካባቢዎች ላይ ተንቀሳቅሶ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ተግባራትን ለማከናወን ያስችለዋል ነው ያሉት::

በመልሶ ግንባታና ማገገም ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሠላም ስምምነቱ ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረ የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ በሚደረገው እንቅስቃሴ የዓለም ባንክ ድጋፍ ያደርጋል:: በሂደቱ ዙሪያ ከመንግሥት ጋር ምክክር እየተደረገ እንዳለም ገልጸዋል::

ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የሠላም ስምምነት ትግበራዎች አዎንታዊ ውጤቶች መታየታቸውን በመግለጽ፤ ሠላሙ ለግሉ ዘርፍ የቢዝነስ ተሳትፎ ዕድል የሚሰጥ እንደሆነም አመልክተዋል:: ባንኩ በተለይም በመሠረተ ልማትና መሠረታዊ አገልግሎት ዙሪያ በሚደረጉ ሥራዎች ድጋፉን እንደሚያጠናክር ገልጸዋል::

ኮቪድ-19፤ በሰሜኑ ግጭትና በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩንና የልማት ዘርፎች ላይ ያለውን አዎንታዊ ግስጋሴ መጉዳቱን ጠቅሰዋል:: ኢትዮጵያ ወደ ፊት መልካም ዕድሎች ያሏት አገር እንደሆነች በጉብኝታቸው ወቅት ማየታቸውን አስታውቀዋል::

አገሪቱ ወደ ጠንካራ የእድገት ጎዳና በመመለስ ለሕዝቦቿ የተሻለ ነገን ለማስረከብ ዕድሉ አላት ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ የሰብአዊ እርዳታ ማድረስ እና በሰሜን አገልግሎቶች ወደ ነበሩበት መመለስ ወሳኝ እና አበረታች እንደሆኑ ተናግረዋል:: ሰላሙ በዘላቂነት እንዲቀጥልና በግጭት የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን አንስተዋል:: የርሳቸው ጉብኝትም ባንኩ በምን መልኩ መደገፍ እንዳለበት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው ብለዋል::

በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግሥት የግሉ ዘርፍ ዕድገትና ኢንቨስትመንትን በማመቻቸት፣ በቁልፍ ዘርፎች የላቀ አቅምን በማጎልበት የጀመረውን ትልቅ የኢኮኖሚ ሪፎርም አድንቀዋል:: የሪፎርም መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያ ካጋጠሟት በርካታ ተግዳሮቶች ለመቋቋም አስቻይ ነው ብለዋል:: ለዚህም ውጤታማና የተፋጠነ እንዲሁም ሁሉን አቀፍ እድገት ማምጣት ይጠበቃል ሲሉ ገልጸዋል::

የዓለም ባንክም ከአገሪቷ ጋር ያለውን የረጅም ጊዜ ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥልና ፖሊሲ ተኮር ድጋፍ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን አመልክተዋል:: ከዚህ ባሻገር ዓለም ባንክ በአፍሪካ እየተፈጠረ ያለውን ነፃ የንግድ ቀጣና እንደሚያበረታታ ጠቅሰዋል:: ይኸውም የአገሪቱን ኢኮኖሚ ይበልጥ የሚያበለጽግ እንደሆነ ተናግረዋል:: ባንኩም ዕሳቤውን እንደሚቀበለውና በትብብር ለመሥራት ዝግጁ እንደሆነ ገልጸዋል::

በጉብኝታቸው ወቅት ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትን ጨምሮ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ፖሊሲ አውጪዎች፣ አጋር ድርጅቶች ጋር መወያየታቸውንና አገሪቷ በርካታ ፈተናዎችን በማሸነፍ ወደ ሁለንተናዊና ቀጣይነት ወዳለው የልማት ጉዞዋ የምታደርገውን ጉዞም ዓለም ባንክ አጋርነቱን ሊያሳይ የሚችልባቸው ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን አንስተዋል::

# በኢትዮጵያ ለእርሻ ከሚውለው መሬት ሰባት ሚሊዮን ሄክታሩ አሲዳማ ነው

## - አራት ሚሊዮን ሄክታር አሲዳማ መሬት ማምረት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ለእርሻ ከሚውለው መሬት ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት አሲዳማ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። አሲዳማ ከሆነው ከሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬቱ ውስጥ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሕክምና ባለማግኘቱ ማምረት የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ ተጠቁሟል::

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የአፈር ሀብት ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሊሬ አብዩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ለእርሻ ከሚውለው መሬት 28 ነጥብ 1 በመቶ በእንክብካቤ እጦት የተነሳ አሲዳማ ሆኗል:: ይህም በምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጸእኖ እየፈጠረ ይገኛል::

ኢትዮጵያ ለእርሻ ከምትጠቀምበት የመሬት ሀብት ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት አሲዳማ ነው ያሉት አቶ ሊሬ፤ አሲዳማ መሬት ባለመታከሙ ምክንያት ኢትዮጵያ ማግኘት ካለባት ምርት ግማሹን እያጣች ይገኛል። መሬቱ ቢታከም አገሪቱ አሁን ከምታመርተው ምርት ከ50 እስከ 100 በመቶ ዕጥፍ ማምረት ትችላለች ብለዋል።

ለአብነትም አሁን ላይ 10 ኩንታል ማምረት የሚችል መሬት አሲዳማ ባህሪ ባለው አፈር የተነሳ ወደ 5 ኩንታል ሊቀንስ እንደሚችል ጠቁመው፤ በአንዳንድ አካባቢዎች አሲዳማ መሬቱ በፍጥነት ሕክምና ካላገኘ ጉዳቱ እየባሰ እንደሚሄድ አመልክተዋል።

እስካሁን በተሠራው ሥራ 110 ሺህ ሄክታር መሬት ብቻ በኖራ ሕክምና ወደ ምርታማነት መመለሱን ገልጸው፤ ከአጠቃላዩ በአሲዳማነት ከተጠቃው አፈር ሕክምና የተሰጠው ሦስት በመቶ ብቻ እንደሆነ አስታውቀዋል።



የግብርና ሚኒስቴር ላለፉት ዓመታት አሲዳማ መሬትን በኖራ የማከም ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ያስታወሱት አቶ ሊሬ፤ ውጤቱ አጥጋቢ አለመሆኑን አቶ ሊሬ ገልጸዋል::

ለዘርፉ የሚበጀተው በጀትና የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን፣ ተከታታይነት ያለው የኖራ አቅርቦት ማነስና የዋጋ መወደድ የአሲዳማ መሬትን ለማከም የሚከናወኑ ሥራዎችን ይበልጥ ውጤታማ እንዳይሆኑ ማድረጉን ጠቁመዋል። በአሁኑ ጊዜም አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሕክምና ባለማግኘቱ ማምረት የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን አስታውቀዋል:: ችግሩም በምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስ ተናግረዋል።

አንድ ሄክታር አሲዳማ መሬትን ለማከም በትንሹ 30 ኩንታል ኖራ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ሊሬ፤ በገንዘብ ሲተመን ከትራንስፖርት ወጪ ጋር ለአንድ ሄክታር መሬት እስከ 31 ሺህ ብር ያስፈልጋል። ይህ ዋጋ ለአርሶአደሩም ሆነ ለመንግሥት ከባድ ነው ብለዋል።

በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሲዳማና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች በአፈር አሲዳማነት የተጠቁ በርካታ አካባቢዎች ያሉባቸው ክልሎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በዘንድሮ ዓመት 200 ሺህ ሄክታር አሲዳማ መሬት ለማከም ታቅዷል። ለዚህም ሥራ በአማካይ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ኖራ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የኖራ ዋጋ ተለዋዋጭ ቢሆንም ለዚህም የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን ወደ 45 ቢሊዮን ብር እንደሚደርስ አስረድተዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ በርካታ የፋይናንስ ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥረት ከማድረግ ባለፈ የተዘዋዋሪ ፈንድ መመሪያ ተዘጋጅቶ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው:: በተጨማሪ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም መሬትን የማከም ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

በተጨማሪ በዚህ ዓመትም በየደረጃው ያለውን አመራርና አርሶአደር ባሳተፈ መልኩ የአፈር ለምነትንና ጤንነትን ማስጠበቅ የሚያስችል የግንዛቤ ለማዘጋጀት ጥረት መደረጉን ጠቁመዋል።

# በአማራ ክልል የ67...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በሌላ በኩልም ጉዳት በደረሰባቸው አራት መምህራን ኮሌጆች ውስጥ በ16 ሚሊዮን ብር ቤተመጻሕፍትን መልሶ የማደራጀት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህም ባለፈ የአማራ ልማት ማህበርን ጨምሮ ሌሎችም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በጥገናና መልሶ ግንባታ ሥራዎች እየተሳተፉ መሆኑን አመልክተዋል::

ሦስተኛውን ዙር ጦርነት ሳይጨምር ከአራት ሺ ሰማኒያ ስድስት በላይ ትምህርት ቤቶች የተለያየ መጠን ጉዳት ደርሶባቸዋል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ከዚህ ውስጥ አንድ ሺ 150 የሚሆኑት ሙሉ በሙሉ የወደሙ ናቸው:: በሦስተኛው ዙር ጦርነትም ከ500 በላይ ትምህርት ቤቶች ጉዳት ደርሶባቸዋል::

የደረሰው ጉዳት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ ያሉ ትምህርት ተቋማትን፣ የትምህርት በሬዲዮ ማሰራጫዎችንና መጋዝኖችን የሚያጠቃልል መሆኑን አስታውሰው፤ የሦስተኛውን ዙር ጦርነት ሳይጨምር በትምህርቱ ዘርፍ ብቻ ስድስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ያህል ጉዳት መድረሱን በጥናት ተረጋግጧል ብለዋል::

መንግሥትና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ባለፈ ማኅበረሰቡን በማስተባበር ትምህርት ቤቶችን መልሶ የማስጀመር ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ እንደ ክልል 500 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች አሁንም ድረስ አልተከፈቱም:: በዚህም ምክንያት አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጪ ሆነዋል::

ከመልሶ ግንባታ ሥራዎች ጎን ለጎን የሥነልቦና ሥልጠና እየተሰጠ መሆኑን ጠቁመው፤ በሁሉም መልኩ ከግብረሰናይ ድርጅቶች እየተሰጠ ያለው ድጋፍ ግን ከደረሰው ጉዳት አንጻር ሲታይ አነስተኛ ነው ብለዋል::

በጦርነቱ ከደረሰው ጉዳት ባለፈ ከተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው የመጡ ዜጎች መበራከትም ከግጭት ቀጣና ውጪ ባሉት ትምህርት ተቋማት ላይ ጫና እየፈጠሩ መሆኑንም ጠቁመው፤ ክልሉ ቀድሞውንም በትምህርት ቤቶች ዙሪያ በርካታ ችግር የሚስተዋልበት መሆኑ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል ነው ያሉት::

እስካሁን በመልሶ ግንባታ ሥራዎች፣ የሥነልቦና ሥልጠና በመስጠትና ለተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ በማቅረብ ተሳትፎ ያደረጉትን ባለድርሻ አካላት አመስግነው፤ ከችግሩ ስፋት አንጻር አሁንም ሰፊ ሥራ የሚጠበቅ በመሆኑ መንግሥታዊና ግብረ ሰናይ ድርጅቶችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የተጠናከረ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል::

# ኢጋድ የኢትዮጵያ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ዋና ጸሐፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ትናንት ድጋፉን ለኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ሲያስረክቡ እንደገለጹት፣ መንግሥት በአገሪቱ ውስጥ የተከሰተውን የድርቅ አደጋ ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ ነው:: በዚህም ኢጋድ መንግሥት ድርቅን ለመቋቋምና ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት ይደግፋል::

በአቶ ወርቅነህ ገለጻ፣ ድጋፉ በስምንቱ የኢጋድ አባል አገራት ስም አጋርነትን ለመግለጽ የተደረገ ነው ብለዋል:: በተለይም በኢትዮጵያ፣ በኬንያ እና በሶማሊያ የድርቅ አደጋ መከሰቱን አውስተው፤ በኢትዮጵያ የሰው ሕይወት ሳይጠፋ እየተደረገ ያለው ርብርብ የሚደነቅ ነው:: አሁንም በዘላቂነት ችግሩን ለመቅረፍ የጋራ ርብርብ እንደሚጠይቅ አመልክተዋል::

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው ኢጋድ በአፍሪካ ቀንድ ያለውን ችግር ለመፍታት ኢትዮጵያን ጨምሮ ለአባል አገራት አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ነው:: በተለይም አባል አገራቱ ችግር ሲያጋጥማቸው የልማት አጋሮችን በማስተባበር በዘላቂነት ከችግር ውስጥ እንዲወጡ የሚያስችል ሥራዎችን የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል::

የክልሉ መንግሥትም ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመተባበር በድርቁ ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን አመልክተዋል። የድርቅ አደጋን በዘላቂነት ለመቋቋም ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ ያሉ ግድቦችን በመገንባት የዘላቂ ውሃ አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖር እየተሠራ መሆኑንም ነው አቶ ሽመልስ የጠቆሙት።

የክልሉ መንግሥት በድርቁ ምክንያት የሰው ነፍስ እንዳይጠፋ የዕለት ደራሽ ምግብ በማቅረብ ላይ መሆኑን በመግለጽ፤ ኢጋድ ላደረገው ድጋፍ ፕሬዚዳንቱ ምስጋና አቅርበዋል::

ኢጋድ በክልሉ ለተከሰተው ድርቅ ከአራት ሚሊዮን 291 ሺህ ብር በላይ ድጋፍ ማድረጉ ታውቋል::

# «የጉራጌ ሕዝብ ችግሮችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የጠቀሱት ነዋሪዎቹ፣ እነዚህ አካላት ተለይተው ለሕግ እንዲቀርቡም ጠይቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ በምላሻቸው በሁሉም አካባቢዎች በርካታ የመልማት ጥያቄዎች መኖራቸውን ገልፀው፤ መንግሥት ያሉትን አቅሞች በማሰባሰብ ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል። ከዚህ አኳያ መንግሥት የጉራጌ ዞን ነዋሪዎች ላነሷቸው የልማት ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ምላሽ ለመስጠት በቅንጅት ይሠራል ብለዋል። ከሕዝቡ ለተነሱት የልማት ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ረገድ ባለሀብቶችም የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

አስተዳደራዊ አደረጃጀት ለጥያቄዎች ሁሉ መልስ መስጫ መፍትሔ አለመሆኑን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የጉራጌ ዞን ነዋሪዎች ከአጎራባች ዞኖች ጋር ያላቸውን አብሮነት በማጠናከር በጋራ ለመልማት መሥራት አለባቸው ብለዋል። የሚነሱ ጥያቄዎችን በሰለጠነና በሰከነ አግባብ መፍታት እንደሚገባም ጨምረው መግለጻቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## መኀልዩ መኀልዩ ዘ "እናት ምድር ባለውለታ"

ሎሬት ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረእግዚአብሄር ባለፈው ሳምንት በ83 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ የሚለው መርዶ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ልብ ያለ ልዩነት የሰበረ ከመሆኑ ባሻገር በማህበራዊም ሆነ በመደበኛው ሚዲያ ሰፊ ሽፋን ማግኘቱ አገር ትልቅ ባለውለታዋን ለማጣቷ ህያው ምስክር ነው። ታዋቂው የብዝሃ ሕይወት ሳይንስቲስት ሎሬት ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረእግዚአብሄር ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው እንደተሰማ መላው ኢትዮጵያዊ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሀዘኑን ገልጿል። ሎሬት ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ባደረባቸው ሕመም በአገር ውስጥ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በ83 ዓመታቸው ባለፈው ሰኞ መጋቢት 11/2015 ለማክሰኞ አጥቢያ 9፡00 ላይ በሞት መለየታቸውን ቤተኛው ደራሲ እና ጋዜጠኛ ዘነበ ወላ አስታውቋል።

ዶክተር ተወልደ ብርሃን በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ አገልግሎት የተከበረ ሥም ያላቸው ሲሆን፤ በዘርፉ ላደረጉት ምርምር እና በጉዳዩ ዙሪያ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲፈጠር ላደረጉት ጥረት በፈረንጆቹ 2000 (Right Livelihood Award) ሽልማትን አግኝተዋል። በተጨማሪም፣ በፈረንጆቹ 2006 ዓመት የተባበሩት መንግሥታት በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች የሚሰጠውን Champions of the Earth ሽልማት አግኝተዋል። ከተማሩበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በ1997 የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ተቀብለዋል። ሎሬት ዶ/ር ተወልደ ብርሃን የሦስት ሴቶች ልጆች አባት ሲሆኑ ከ60 በላይ ሌሎች ልጆችን ያሳደጉ ልበ ቀና ሰው እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። ታዋቂው የአካባቢ ጉዳይ ሳይንስቲስት ዶክተር ተወልደ ብርሃን ገብረእግዚአብሄር የደራሲ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ታናሽ ወንድም መሆናቸው ይታወሳል ይለናል ሰሞኑን በስፋት በማህበራዊ ሚዲያ ሲዘዋወር የተመለከትሁት መርዶ።

መኃልየ መኃልይ ዘሰሎም ከሁሉም የሚበልጥ የሰለሞን መዝሙር ማለት ነው። የሁለት ፍቅረኛዎች ንግግር ተደርጎም ይወሰዳል። የፍቅረኞች ንግግር በግጥም ነውና ምት፣ ዜማ አለው። ሰለሞን ስለ ሙሽራውና ሙሽሪት፣ ስለፈጣሪና ስለ ቤተ ክርስቲያን የዘመራቸውን 1ሺህ 5 መዝሙሮችን ይመለከታል። ሙሽራው ልዑል እግዚአብሔርን ሲወክል ሙሽራይቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። መኃልይ እንደ ለዘብና ወረብ አይነት በፍጥነት የሚዘመር ጥዑም መዝሙር ነው። መዝሙሮቹ በተለያየ ስልት ዜማ ቢደጋገሙም ያው ስለፈጣሪና ቤተ ክርስቲያን ክብር፣ ቅድስና የሚመስክሩ ናቸው። ይህ መጣጥፍ ስለ ዶ/ር ተወልደብርሃን ገብረ እግዚአብሔር፤ የሚዘክር፣ የሚያወድስና የሚያከበር ሆኖ ስለአገኘሁት" መኃልዩ መኃልዩ ዘ "እናት ምድር ባለውለታ"ማለትን መርጫለሁ።

ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር የካቲት 11 ቀን 1936 ዓ.ም ትግራይ ተወልደው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተወለዱበት አካባቢ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በጄነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። እንዲሁም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በባይሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በከፍተኛ ማዕረግ የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ አጠናቀዋል። በመቀጠል ወደ እንግሊዝ ሄደው ከዌልስ ዩኒቨርሲቲ በዶክትሬት ዲግሪ ተመርቀዋል።

ከዚያም በ1961 ዓ.ም ወደ አገራቸው ተመልሰው በዩኒቨርሲቲ መምህርነትና በሳይንስ ፋኪልቲ ዲንነት፣ ሰርተዋል። ወደ አስመራ ዩኒቨርሲቲ ተልከው በፕሬዚዳንትነት ለስምንት ዓመታት በከፍተኛ ኃላፊነት መርተዋል። ከ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ በኋላም የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ስትራቴጂ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ቀጥሎም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ለአገር የሚጠቅሙ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል።

ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረእግዚአብሔር በሥነ ሕይወትና በአካባቢ ጥበቃ ላይ ከ30 በላይ ጥናቶችን በማሳተም፣ የአካባቢ ጥበቃ ስትራቴጂ በመቅረጽ፣ የሥነ ሕይወት ሀብታችንን የሚገልጹ መጽሐፎችን በማሳተምና በመሳሰሉት ለአገርና ህዝብ የሚጠቅሙ ተግባራትን አከናውነዋል። ከዚህ አልፈው በአፍሪካ ኅብረት ውስጥ ማኅበረሰብ፣ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች የሥነ ሕይወት ሀብት ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ሕግ በተጨማሪም የአፍሪካን የባዮ ቴክኖሎጂ ሴፍቲ ሕግ በማርቀቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃም አገራችንንና አፍሪካን በመወከል በብዝኃ ሕይወትና በአካባቢ ጥበቃ ላይ በተመረኮዙ የተለያዩ ድርጅቶች ላይ በግንባር ቀደምትነት ተሳትፈዋል። በተለይ ጂ 77 ተብለው ለሚታወቁ አገሮች ዋንኛ ተከራካሪ ሆነው በመሪነት በተጫወቱት ሚና በሥነ ሕይወት ደኅንነትና ብዝኃ ሕይወት ጥበቃ እንዲከበር፣ ታዳጊ አገሮች አገር በቀልና የማህበረሰብ መብቶች እንዲከበሩ ሽንጣቸውን ገትረው ተከራክረዋል። በታሪክ የተመዘገቡ ውጤቶችንም አስመዝግበዋል።

ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገ/እግዚአብሔር በአገራችን የአካባቢ ሥነ ሕይወትና ብዝኃ ሕይወት ጥበቃ ጉዳይ ሲነሳ ከማንም በላይ በታላቅ ክብር ስማቸው የሚነሳ የተከበሩ ሳይንቲስት ናቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃም በብዙ የምርምርና የትምህርት ተቋማት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ታዋቂ ሰዎች ዘንድ የከበረ ስም አትርፈዋል። በተሰማሩበት መስክ የአገርንና የህዝብን ጥቅም በማስቀደም በተለይም የአርሶ አደሮችና የአርብቶ አደሮች ጥቅም እንዲጠበቅ በቁርጠኝነት ጠንክረው ሰርተዋል።

በተዳቀሉ እህሎች በእርዳታ ሰበብ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡና ትውልድ እንዳይበላሽ በዓለም አቀፍ መድረኮች ጭምር ተከራክረዋል። በአጭር መግለጫ ተገልጾ በማያበቃው ሥራቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ የክብር ሽልማቶችን አግኝተዋል። ከዚህም ውስጥ እኤአ በ2006 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የአካባቢ ጥበቃ ሽልማት "የምድር ሻምፒዮን"ተብለው ተሸልመዋል። ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ለአገርና ለህዝብ በሚጠቅሙ የላቁ ተግባሮቻቸው የተነሣ መንግሥታዊ ኃላፊነትን በመወጣት ዘርፍ የ2008 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት አሸናፊ መሆናቸው አይዘነጋም።

ዶክተር ተወልደ ብርሀን ገብረእግዚአብሔር የብዝሀ ሕይወት ጉዳይ የሚገዳቸው፤ በዓለም አቀፍ መድረኮች በማደግ ላይ የሚገኙ 134 አገራትን ወክለው የተደራደሩ ሳይንቲስት ነበሩ። ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ዶክተር ተወልደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና አስመራ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለያዩ ተቋማት በሙያቸው አገልግለዋል። የአካባቢ ጥበቃ ህይወት ሳይንቲስት የነበሩት በርካታ ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ሽልማቶችን ባለቤት ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር ለአገራችንም ሆነ ለዓለም አርሶ አደሮችን መብት ያስከበሩ የዘረ መል ማሻሻያ በተደረገባቸው ወይም የGMO ምግቦች ያላቸውን ተጽዕኖ አስመልክተው ውጤት ያለው ድርድር ያደረጉ ሳይንቲስት ነበሩ። በሥነ-ምህዳር ሳይንስ አያሌ ምሁራን ለዓለም ያፈሩ እንዲሁም በርካታ መጽሃፍትን በመጻፍ፣ የአካባቢ ጥበቃ ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ለአገር ያበረከቱ ሳይንቲስት ነበሩ።

**የዶ/ር ተወልደብርሀን ሀሳብ ተሰሚነት አግኝቶ ቢተገበር ኖሮ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ለማዳበሪያ ግዢ በቢሊዮን የሚገመት ወጪ አታወጣም ነበር**

የ83 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ የነበሩትን ሳይንቲስት ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር ከአራት አስርት ዓመታት በላይ እንደሚያውቋቸው ለዶቼ ቬሌ የተናገሩት ፕሮፌሰር እንዳሻው በቀለ ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ተቋምን ብቻ ሳይሆን አብረው ሰው የመሰረቱና ያፈሩ ትልቅ ሰው ናቸው ሲሉ በአገራችን ይሁን በአህጉር ደረጃ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ናቸው ብለዋል። ካበረከቱት ስራዎች መሀከል ጥቂቶቹን አካፍለውናል።

«ባደጉት አገሮች መሀከል ያለውን የብዙሃ ህይወት አጠቃቀም እና የመካፈል ወይንም አብሮ ቀጣይነት እድገት ላይ ለመስራት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው።» አያይዘውም «የአፍሪቃ አገሮች አስተባብሮ የተሟገተ ተሟግቶም ያሸነፈ በመጨረሻም አፍሪቃ የራስዋን እንብዛ ህይወት እንድትጠብቅ ያደረገ ሰው ነው» በአገራችንም ቢሆን ይላሉ ፕሮፌሰር እንዳሻው «በኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ላይ ብዙ ህጎች እንዲወጡ በአየር ለውጥ ኢትዮጵያ ታወቂ ሆና አቅሟ እንዲጎለብት ያደረገ ትልቅ ሰው ነበር » ብለዋል።

የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያው ዶክተር ተወልደ ብርሃንን ስራዎች «የምድራችን ጀግና» በሚል በመጽሀፍ ያሳተመው ደራሲ ዘነበ ወላ ዶክተር ተወልደ ብርሃን በብዙሃን ህይወት ሀብት ላይ አፍሪካን ወክለው በዓለም መድረክ ላይ ይቀርቡ ነበር ሲል ለዶቼ ቬሌ ተናግሯል፤ የሚያውቁትም ይሁን የማያውቁት ሰው ሲስቅ ማየት ከምንም ነገር በላይ ያስደስታቸዋል ያለው ደራሲ ዘነበ፤ የብዙዎች አባት ነበሩ ሲሉ ስለአገራቸው የነበራቸውን ስሜት በዚ መልክ አጋርተውናል።

«ከምንም ነገር በላይ የሚያሳስበው የኢትዮጵያ አንድነት ነው» በጣም ብዙ ስራዎች ሰርተዋል ከነዚህ መሀከል ይላሉ ደራሲው «ኢትዮጵያ ከማዳበሪያ ገበያ ነጻ የሆነች አገር ለመፍጠር ያለፉትን 30 ዓመታት ጥረት አድርገዋል። ሌላው የማህበረሰብ መብት ና የዓለም አርሶ አደሮች መብት ላይ ነው በብዙሀን ህይወት ላይ የባለቤትነት መብት ማውጣት ጀምረው ነበር ሌላው ሰው የፈጠረው ቁሶች ላይ ማውጣት ይቻላል በህያውያን ላይ ግን ማውጣት ገበሬውን እንደሚጎዳው ስለሚያውቅ ባደረገው ከባድ ክርክር ለውጤት አብቅቷል » ብለዋል።

ያስገኙትን ውጤት ሲናገሩ « በዓለም ላይ ከ1 ነጥብ 4 ቢሊዮን በላይ አርሶ አደሮችን የዘር መብት ባለቤትነታቸውን አረጋግጠዋል» ብለዋል። ደራሲ ዘነበ ወላ ለበርካቶች አባት እና መጠለያ የነበሩት ዶክተር ተወልደ ብርሃንን የሕይወት ጉዞ ዙሪያ ዳሰስ ያለ መጽሐፍ አሳትመዋል ብለዋል።

ዶክተር ተወልደ ብርሃን የዩናይትድ ኪንግደም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ጨምሮ በተለያዩ መድረኮች በመገኘት አካባቢ ጥበቃና ሥነ ህይወት የተመለከተ ንግግሮችን አድርገዋል በርካታ ስራዎችንም ለዓለም አበርክተዋል ያሉት ፕሮፌሰር እንዳሻው በቀለ፤ ዶክተር ተወልደ ብርሃን ሳይንሱን በአገራችን ለማበልጸግ ትልቅ ስራ ሰርተዋል ይላሉ። «ሳይንሱን ለማበልጸግ ትልቅ ስራ ነው የሰራው። ትልቅ ሰው ነው። ብዙ የሰራ ሰው ነው በፍሎራው በኢኮሎጂው፤ በቬጂቴሽን ለምሳሌ በደርግ ግዜ በጋምቤላ እና ዴዴሳ ኢኮሎጂው ቬጂቴሽን አሰርቷል ግን እሱ እንደሰራው አድርገን አይደለም የምንመለከተው ወይም ምናገናዝበው ሌላው በባዮ ቴክኖሎጂ ላይ በደንብ እውቀቱ ኖሮት ብዙ ስራዎችን እንዲሰራ ያደረገ ነው ለአገሩ በርካታ ስራዎችን ያበረከቱ ሰው ነው»

ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ከአካባቢ ጥበቃና ብዝሃ ህይወት ጋር የሚያያዝ ከ30 በላይ ጥናቶችን አሳትመዋል። በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መጽሐፍትንም ጽፈዋል እንዲሁም በርካታ ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ሽልማቶችን አግኝተዋል።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር 2000 ላይ ስዊዲን ስቶኮልም በአካባቢ ጥበቃ በነበራቸው አስተዋጽኦ አማራጭ (Alternative) የኖቤል ሽልማት የወሰዱ ሲሆን በ2006 ሲንጋፖር ላይ (champion of the earth) የሚል ሽልማትን ከመንግሥታቱ ድርጅት ተበርክቶላቸዋል።

በዶ/ር ተወልደብርሃን ሕይወት ማለፍ ሐዘኑን ለአሜሪካ ድምጽ የገለፀው የግለታሪካቸው ጸሐፊ ዘነበ ወላ፤ "በአገሩ፣ በወገኑ እና በራሱ ማኅበረሰብ ጥሩ አስተዋፅኦ ካደረጉ እና ተጠቃሽ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው። ዓለም ለወደፊት ስለ አካባቢ ጥበቃ አሳቢዎቿ በምትፅፍበት ጊዜ ከአውራዎቹ አንዱ ዶ/ር ተወልደ ይሆናል። " ብሏል።

በማስከተልም፤"ዶ/ር ተወልደ አንተን የሚተካ ሰው ፈጥረሃል ወይ ብዬ ስጠይቀው፣ እኔ መተካት አለብኝ ብዬ የማስብ ሰው አይደለሁም፣ ማስተማር እኮ ራስህን መተካት ነው" ብሎኛል። የዶ/ር ተወልደብርሀን ሀሳብ ተሰሚነት አግኝቶ ቢተገበር ኖሮ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ለማዳበሪያ ግዢ በቢሊዮን የሚገመት ወጪ አታወጣም ነበር። " ብሎናል።

ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገብረእግዚአብሄር ከእናታቸው ከወ/ሮ ማእዛ ተወልደ መድኅን እና ከአባታቸው ከመምሬ ገብረ እግዚአብሄር ገብረ ዮሐንስ በሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይ ክልል በአድዋ ከተማ አቅራቢያ በምትገኝ ይርባገረድ በተባለች አካባቢ የካቲት 12 ቀን፤ 1932 ዓ.ም ተወልደው በ83 ዓመታቸው መጋቢት 11 ሰኞ ለማክሰኞ አጥቢያ 2015 ዓ.ም አረፉ። የቀብር ስርአታቸው በአዲስ አበባ ከተማ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ባለፈው እሮብ ተፈጽሟል። ዶክተር ተወልደ የሦስት ሴት ልጆች አባት ነበሩ ።

ዓለማቀፉ የሰላም፣ የእርቅ ፣ የሽምግልናና የግልግል ረቡኒ/ መምህር / ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ ዘላቂ ሰላም እውን እንዲሆን ሰው በመጀመሪያ ከፈጣሪ ጋር ከዚያ ከራሱ ጋር በማስከተል ከተፈጥሮ ጋር ሰላም፣ እርቅ ማውረድ አለበት ይላሉ ። ከተፈጥሮ ጋር ሰላም ለመፍጠር የሰው ልጅ ተፈጥሮን እንዳይኑ ብሌን መንከባከብ ይጠበቅበታል። ዶ/ር ተወልደብርሀን የሰውን ልጅ ከተፈጥሮ ጋር የሚያሸማግሉ፣ የሚያስታርቁ አባት ነበሩ።

ምንም እንኳ ስማቸው የኖቤል የሰላም ተሸላሚ እንደነበሩት ኬኒያዊቷ የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋች ዋንጋሪ ማታይ ወይም የእናት ምድር ጠበቃ ስለሆነችውና ከልጅ እስከ አዋቂ ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ፣ ከአገር መሪ እስከ ተራው ዜጋ ፣ ከትምህርት ቤት የአካባቢ ጥበቃ ክበብ እስከ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአጠቃላይ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ስለ የአየር ንብረት ለውጥ ዓለማቀፍ ንቅናቄን እንደ አቀጣጠለችው፤ የኖቤል የሰላም አሸናፊ እጩ፤ የተወዳጁ TIME መፅሔት የ2019 ዓ.ም የዓመቱ ሰው ተብላ እንደተመረጠችው ስዊድናዊት ብላቴና ግሬታ ተንበርግ ባይዘመርላቸውም እናት ተፈጥሮ ግን ውለታቸውን መቼም ቢሆን አትዘነጋውም።

**ሻሎም ! አሜን ፫ ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# መለስካቸው አምሃ፡ ከብስራተ ወንጌል እስከ አሜሪካን ድምፅ

**ሰላማዊት ውቤ**

የዛሬ እንግዳችን በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ስማቸው ጎልቶ ከሚጠቀሱት አንጋፋ ጋዜጠኞች አንዱ ናቸው። ግን ደግሞ በ14 ቋንቋዎች ዜናዎችንና ፕሮግራሞችን በሚያዘጋጅና በመላው ዓለም በሚደመጥ ሬዲዮ ጣቢያ ጋዜጠኛ እሆናለሁ ብለው ፈጽሞ አስበው አያውቁም። ሙያውን አህዱ ያሉት በብዙ አፍሪካ አገሮች እየተዘዋወረ የጋዜጠኝነት ስልጠና በሚሰጥ ዓለም አቀፍ ተቋም ነው። እሳቸው እንዳወጉን ነገሩ እንዲህ ነው፤

ጋዜጠኛ መለስካቸው አምሃ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁበት በተለይም ከ1962 እስከ 1965 የአብዮቱ መዳረሻ ዓመት ድረስ የነበረው ወቅት ከፍተኛ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ነበረበት። ሰዓቱ የከፍተኛ ትምህርትን ቀጥሎ፤ በወጉ አጠናቆ መውጣት እጅግ አስቸጋሪ የሆነበት፤ሥራ የማግኘት ዕድሉም እየጠበበ የመጣበት ነበር። በዚህ ወቅት የኪስ ገንዘብ እየሰጠ የሚያሰለጥን ድርጅት መኖሩን የሰሙት አንጋፋው ጋዜጠኛ ዓይናቸውን አላሹም። ዓላማቸው ሥራ ማግኘት እንጂ ጋዜጠኛ መሆን አልነበረምና አጋጣሚውን ተጠቅመው ገና በታዳጊነት ዕድሜያቸው ወደ ሙያው ገቡ። የገቡት ይሄው በብዙ አፍሪካ አገሮች እየተዘዋወረ የጋዜጠኝነት ስልጠና የሚሰጥ ዓለም አቀፍ ተቋም በሰጣቸው የስልጠና ዕድል በመታገዝ ነው።

ከገቡበት በኋላ ሙያውን እጅግ እየወደዱት በመምጣታቸው ዛሬም ከአራት አሥርት ዓመታት በላይ ድረስ ጽኑ ፍቅሩ ሙጥኝ ስላላቸው መውጣት አልሆነላቸውምና በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ፕሮግራም በርካታ ሥራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ። ሥራዎቻቸው ሰው ሰው፤ የሚሸቱ ሰብአዊነትንና እኩልነትን የሚሰብኩ፤ብልሹ አሰራሮችን አጥብቀው የሚያወግዙና የሚያጋልጡ ናቸው። በአድማጭ ዘንድም ሰፊ ተደማጭነት፤ ተወዳጅነትና አድናቆትን አትርፈውላቸዋል።

አሌፍ መጽሔት፤ ደወል ጋዜጣ እና አዲስ ዜና ጋዜጣን ከመመስረት ባሻገር እነዚህን ተንተርሰው በግላቸውና በጋራ በትልቅ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዘርፍ የመሰማራት ራይም ሰንቀው ሲንቀሳቀሱ የቆዩባቸው ጊዚያት ብዙ ናቸው። ቢሆንም አፈናና እስሩ አላዘለቃቸውም። ይሄ ዛሬም ድረስ ቅሬታ ቢያሳድርባቸውም በአካላቸው ላይ የደረሰ ጉዳት እንዳልነበረ ይናገራሉ። ቢሆንም የዛሬው እንግዳችን መለስካቸው አመኃ በብርቱው በትር ተማረውና ተሰላችተው ከሙያው ሳይወጡ አሁንም በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ እያገለገሉ የሚገኙበትን ተመክሮ እንድትጋሩ እንጋብዛለን፤

### ልደት፣ እድገትና ትምህርት...ማንነት

የተወለዱት በ1944 ዓ.ም በቀድሞው አጠራር ጎጃም ጠቅላይ ግዛት ነው። ዕድገታቸው ደግሞ ኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ጎሬ ከተማ ሲሆን አሁን ላይ 71 ዓመታቸውን ለመያዝ መንገድ ላይ ናቸው። ቤተሰብ ከመሠረቱ በጣም ረጅም ጊዜ ሲሆናቸው ሁለት ሴቶች ልጆች ወልደዋል። የልጅ ልጆች በማየት ዛሬም ከእኝሁ የመጀመሪያ ትዳር አጋራቸው ጋር በፍቅር አብረው ይኖራሉ። በጋዜጠኝነት ሙያ ከ40 ዓመታት በላይ ዓለም አቀፍ እውቅና ባለው ተቋም አገልግለዋል። አንድ ሁለቴ ከሙያው ወጥተው የነበረ ቢሆንም ብዙም ሳይቆዩ በመመለስ አሁንም በጋዜጠኝነቱ ሙያቸው በአሜሪካን ድምፅ ራድዮ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። እስከ ስምንተኛና (መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ) ያለውን በጎሬ አቡነ ሚካኤል እና በቀዳማዊ ሃይለስላሴ ትምህርት ቤት ተምረዋል። እስከ 12ኛ ክፍል የነበረውን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት ደግሞ አዲስ አበባ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ነው።

የከፍተኛ ትምህርታቸውን የቀጠሉት ወደ ሥራ ዓለም ከገቡ በኋላ ዘግየት ብለው ሲሆን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካ ሳይንስ እና አለማቀፍ ግንኙነቶች ተመርቀዋል። በተጨማሪም በአገር ውስጥ፣ እንዲሁም በአፍሪካ እና ወደ ተለያዩ የአውሮፓ አገሮች በመጓዝ እየተዘዋወሩ በርካታ የጋዜጠኝነት ሙያ ኮርሶችን በመውሰድ ራሳቸውን በሙያው አበልፅገዋል። በተለይም በአዲስ አበባ፣ በናይሮቢ በኖርዌ-ክርቲነሳንድ- በነበረው ስኩል ኦፍ ጆርናሊዝም ኤንድ ኮሚዩኒኬሽንስ ባገኙት ስልጠና ዲፕሎማ ይዘዋል። እንዲሁም ተመሳሳይ ሙያዊ ስልጠና ያገኙበትና በየደረጃው ሙያዊ ብቃትና ችሎታቸውን እያሻሻሉ የመጡባቸው ብዙ ናቸው።

ከላይ እንደተገለፀው፣ እንግዳችን በተለይ የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን የጨረሱበት ከ1962 እስከ 1965 የነበረው የአብዮቱ መዳረሻ ዘመን ከፍተኛ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የነበረበት ነበር። በዚህ ዘመን ትምህርት ቀጥሎ በወጉ አጠናቆ መውጣት እጅግ ይፈትናል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ማጠናቀቅ በራሱ ዕድለኛ የሚያስብል ነው። ሥራ የማግኘት ዕድልማ እየጠበበ በመምጣቱ ፈፅሞ የሚታሰብ አልነበረም።

### ወደ ሙያው የገቡበት አጋጣሚ

አቶ መለስካቸው እንደሚሉት ያኔ እንደ ዛሬው የጋዜጠኝነት ትምህርት ቤት አልተከፈተም። በመሆኑም መደበኛ የጋዜጠኝነት ትምህርት የሚባል አልነበረም። በዚህ ውስጥ እየኖረ ያለ እንደሳቸው ያለ ታዳጊ ወጣት ታዲያ ጋዜጠኛ እሆናለሁ ብሎ ይመኛል ማለትም ዘበት ነው። ጋዜጠኛ እሆናለሁ ብሎ ጭራሽ በልቡ ባያልመውም አይደንቅም። የአብዮቱ መዳረሻ ዘመን 12ኛ ክፍልን አጠናቅቆ ሥራ መቀጠር የማይናፍቅ ወጣት ግን አልነበረም። መለስካቸው አመሃ ከነዚህ ዓይነት ወጣቶች አንዱ ነበሩ። የኪስ ገንዘብ እየሰጠ በጋዜጠኝነት የሚያሰለጥን ድርጅት መኖሩን የሰሙትም በዚህ ወቅት ነው። ይሄ ዜና ለያኔው ታዳጊ መለስካቸው አመሃ ትልቅ ዕድልና መልካም አጋጣሚ ነበር። በመሆኑም በዕድሉ ለመጠቀም በመሮጥ የቀደማቸው አልነበረም።

‹‹ቢሆንም አጋጣሚውን ተጠቅሜ ሥራ ላግኝ እንጂ ጋዜጠኛ እሆናለሁ ብዬ አይደለም። ጋዜጠኝነት ጨርሶ፣ በልቤ አስበውና አልመው የነበረ ሙያ አልነበረም። ዕድሉ ግን ለኔ መልካም ነበርና በ1966 ዓ.ም በ14 ቋንቋዎች ዜናዎችንና ፕሮግራሞችን በሚያዘጋጅ በመላው ዓለም የሚደመጥ ሬዲዮ ጣቢያ ተቀላቀልኩ›› ሲሉም ድንገተኛ አጋጣሚውን ከአራት አሥርት ዓመታት በላይ ወደኋላ ተጉዘው ያስታውሱታል።

### ስልጠና

ዕውቁ ጋዜጠኛ መለስካቸው አምሃ በ1966 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ የተቀላቀሉት በብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ 14 ቋንቋዎች ዜናዎችንና ፕሮግራሞችን የሚያዘጋጅ በመላው ዓለም የሚደመጥ ሬዲዮ ጣቢያ ነው። ያስተዳድረው የነበረው ወርልድ ሉተራን ፌዴሬሽን ነበር። በሥሩ መካነ ኢየሱስ፣ የምስራች ድምፅ የሬድዮ እስቱዲዮ ነበርና በዚሁ ውስጥ በመግባትም ለሁለት ወራት ያህል በጋዜጠኝነት ሙያ ሰለጠኑ። በስልጠናውም መሠረታዊ የሆነ የሬዲዮ ፕሮግራም አዘገጃጀቶችን ተምረዋል። ስልጠናውን የሰጧቸው በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ወ/ሮ ዓለም ሰገድ ኀሩይ እንደነበሩ ያስታውሳሉ። ዓለምሰገድ በተለያዩ ዓለም አገራት እየሄዱ በማሰልጠን ከፍተኛ ልምድ የነበራቸው ተግባቦታቸውም መልካም በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከመሰረታዊ ጋዜጠኝነት ትምህርት ያለፈ ዕውቀት እንዲቀስሙ ያስቻላቸው መሆኑንም ያነሳሉ። ወ/ሮ ዓለም ሰገድ ብቻም ሳይሆኑ ከፍተኛ የሞያ ብቃት የነበራቸው ከውጭ የሚመጡ አስተማሪዎችም ሌክቸር (ገለፃ) ያደርጉላቸው ስለነበር ከፅንሰ ሃሳብ እስከ ቴክኒኩ ድረስ ትምህርት ለመውሰድ ስመቻላቸውም ያወሳሉ። ‹‹በአጭር ጊዜ ስፋትና ጥልቀት ያለው ስልጠና ለማግኘት ችለናል›› ሲሉ አንጋፋው ጋዜጠኛ መለስካቸው አመሀ ወደሬዲዮ ጋዜጠኝነት የገቡበትን ሁኔታ ያስታውሳሉ።

### የጋዜጠኝነት አሀዱ

ጋዜጠኛ መለስካቸው አምሃ ከስልጠና መልስ ቀጥታ ወደ ሥራ የመሰማራት ዕድል አላገኙም። ወደ ሥራ የተሰማሩት በ1969 መስከረም ላይ ነበረ። “የመጀመሪያው የሥራ ጅማሮዬ የሆነው ፕሮግራም መሥራት ነበር” ይላሉ። እንዳጫወቱን ይሰሯቸው የነበሩ ፕሮግራሞች የተለያዩ መሠረቶች የነበራቸው ነበሩ። ለምሳሌ በወቅቱ ቢቢሲ ላይ በሚቀርቡ ቢቢሲ እስክሪፕት የሚል ርእስ ይዘው በሚመጡ ፅሁፎች የተመሰረቱ ፕሮግራሞችን ነበር የሚሰሩት። ‘ታውቀላችሁን’ በሚል ፕሮግራማቸው ላይ እነዚህን ጽሑፎች በመተርጎም ሥራቸውን ጀመሩ። በወቅቱ አለቆቻቸውና ጓደኞቻቸው ያበረታቱዋቸው ነበር። በዚህ ቀስ በቀስ እየተበረታቱና ሙያውን እየወደዱት የመጡት ጋዜጠኛው ፈጥነው አንዳንድ ሳይንሳዊና እንዲሁም ባሕላዊ የሆኑ፣ ማህበራዊ ጉዳዮችንም ጭምር የሚዳስሱ ሥራዎችን ወደ ማዘጋጀት በተሸጋገሩበት ወቅት ነበር።

‹‹ወደ ኋላም ታውቃላችሁን ከተባለው ፕሮግራም በተጨማሪ ከራሴ አንቅቼ የምሰራው ሌላ ሳምንታዊ ፕሮግራም ማቅረብ ጀመርኩ›› ይላሉ። ”ይህን ዓይነት



ፎቶ- አሸናፊ ጉደታ

ፕሮግራሞች መስራት ያስጀመረን የወቅቱ አለቃችን አቶ የወንድወሰን አለሙ ነበር። እንደማስታውሰው ከሆነ አቶ የወንድወሰን በዚያን ጊዜ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሄዶ ስልጠና ወስዶ ተመልሰዋል፤ እንደተመለሰም መልካም ተመክሮውን ሊያካፍለን ሲል-ስንቶቻችንን እንደሆነ አላስታውስም እንጅ- በየግላችን አንድ ሳምንታዊ ፕሮግራም፣ ርእሱን ጨምሮ ይዘቱንና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሄድ፤ ከነ እቅዱ ዝርዝር ምክረ ሃሳብ (ፕሮፖዛል) እንድናቀርብ አዘዘን። እኛም በዚሁ መሰረት እኔ ‘የስልጣኔ ዕድገት’ የሚል ርእስ ያለው ፕሮግራም ፕሮፖዛል አቀረብኩ። ያቀረብኩት ምክረ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቶ ምናልባት ለአንድ ዓመት ያህል ሲተላለፍ እንደነበረ እና በሌሉሁበትም ለወራት ይተላለፍ እንደነበረ አስታውሳለሁ ይላሉ። ፕሮግራሙ በአብዛኛው በሳይንስና በማህበራዊ ጉዳዮች ያተኮረ ነበር። ዳሰሳው ከዚህም አልፎ የፍልስፍና ጉዳዮችን ሁሉ የሚያካትት ነበረው። ‹‹ይሄን ፕሮግራም የማዘጋጀው የሚመለከታቸውን ምሁራንና ሌሎች ከየአርእስቱ ጋር ቅርበት ያላቸውን ሰዎች በመጠየቅ ነበር›› የሚሉት አንጋፋው ጋዜጠኛ መለስካቸው አመሃ እነዚህን ሰዎች ለማግኘት ብዙ አሰሳ ማድረግና ስለጉዳዩም ለማወቅ ብዙ ማንበብ ያስፈልግ እንደነበረም ያወሳሉ።

### የመጀመሪያው ድንጋጤ

እንግዳችን ሙሉ ጋዜጠኛ መሆንና ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ማግኘት የቻሉበት እንዲሁም በመላው ዓለም ተወዳጅነትን በማትረፍ ሲደመጥ የነበረው ብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ የአብዮቱን ፍንዳታ ተከትሎ ወደ ስልጣን በመጣው የደርግ መንግስት ተወረሰ። ጣቢያውን በ1969 ዓ.ም. መጀመሪያ በየምስራች ድምፅ በኩል ብስራተ ወንጌልን የተቀላቀሉት አቶ መለስካቸው ስልጠናውን እንዳጠናቀቁ በጋዜጠኝነት አልተቀጠሩም። ሥልጠናውን በአንደኛ ማእረግ ቢያጠናቅቁም አንዱ የፊት ጥርሳቸው የወለቀ ስለነበረ አትቀጠርም ተባሉ። ‹‹አትገባም የተባልኩበት ሁኔታን በወቅቱ ለእኔ አሳማኝ አልነበረም፤ ምክንያቱም የተባለው ጉድለት በሬዲዮ ጋዜጠኝነት የማያሰራኝ ከነበረ ስልጠናውንም መውሰድ ሊፈቀድልኝ አይገባም ነበር›› የሚሉት እንግዳችን ‹‹ለካ በኔ ፈንታ በየምስራች ድምፅ ውስጥ ትልቅ ሹም ዘመዱ የነበሩ ሰልጣኝ እንዲገባ ቦታ መልቀቅ ነበረብኝ ››ሲሉ ይገልፁታል።

### ዕድገት በሕብረት

እንግዳችን ዕድገት በሕብረት ዘመቻ የዘመቱት ከዚህ በኋላ ነው። የደረሳቸው አርባ ምንጭ ከተማና ዙሪያው ሲሆን ከልብ የማይወጣ ትዝታ እንዳላቸውይናገራሉ። ‹‹እንዳውም ከማንነቴ አብዛኛው የተቀረፀው በዘመቻው ጊዜ አርባ ምንጭ ላይ ይመስለኛል›› ይላሉም። እንዳከሉት በወቅቱ እሳቸውና ሌሎች ወጣቶች ብዙ ደክመዋል። ገበሬዎችን በማደራጀት፣ መሠረተ ትምህርትን በማስፋፋት፣ በማስተማር፣ የጤና ትምህርት በመስጠት፣ አርሶ አደሩን አደራጅቶ ለመብቱ እንዲታገል በማድረግ ያደረጉት ጥረት ዛሬም የሚጣፍጣቸው ትዝታ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ አስቂኝ ትዝታም አላቸው። ታዲያ ስለዚሁ ትዝታ እንዳጫወቱን ከአርባ ምንጭ በስተምዕራብ ከከተማው ባሻገር የስምጥ ሸለቆው አፋፍ ሆነው የሚነሱት የጋሞ የተራራ ሰንሰለቶች አሉ። ከዛ ደግሞ ወደ ኦሞ ነው የሚወርደው። እዚህ ከሚያደራጁቸው የንዑስ ጣቢያዎች መካከል ዝገቲ የምትባል በጣም ትልቅ ተራራ ውስጥ የምትገኝ መንደር አለች። እናም እዚህ ካደራጁቸው አርሶ አደሮች ያንዱ ቀበሌ ሊቀመንበር የሆኑትና አቶ ካንኮ ሸሌ የሚባሉ ነበሩ፤ እንዲሁም አንድ የፊታውራሪ ማዕረግ የነበራቸው ባላባት ይኖራሉ። የሥራቸው ሂደት በዙር እንደመሆኑ እዚህች ንዑስ ጣቢያ ለአንድ ወር ቆዩ። እነሱ ሲጨርሱ ደግሞ ሌሎቹ ይተኳቸው ነበርና በእነሱ ተራ ጊዜ እኚህ ባላባት እራት ይጋብዟቸዋል። ያደረጉላቸው ግብዣ ትልቅ ነበር። በልተውና ጠጥተውም ይመለሳሉ። ‹‹ታዲያ በማግስቱ አቶ ካንኮ ሌሊት ተነስቶ እኛ ጋ መጣ፣ “ምነው ምን ነካህ በሌሊት ብለን ጠየቅነው። ‹እናንተ ቀን ቀን ፊውዳል እያላችሁ እያስተማራችሁን ማታ ማታ እነሱ ጋ የምትጋበዙበት ምክንያት ምንድነው” አለን ›› ሲሉም አስቂኙን የዘመቻ ትዝታቸውን ያስታውሳሉ። ‹‹ያለው የማይካድ ዕውነት ነበርና ምንም መናገር አልቻልንም›› ይላሉ።

ሁለተኛው አስቂኝ እማይረሳ ገጠመኛቸውም መነሻው ከእዚሁ ከዘመቻ ጋር የተያያዘ ነው። ታንዛኒያ ልክ እንደኛ እድገት በህብረት የሚመስል ‹ኡጃማ› የሚባል የገጠር ልማት ፕሮግራም ነበራትና ደርግ ፕሮግራም አዘጋጅቶ እሳቸውን ጨምሮ የተወሰኑ ሰዎች መርጦ የላከበት መርሃ ግብር ነበር። በተላከው ቡድን ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ኮሌጅ የገቡ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነበሩ። ይሄኔ እሳቸው መደበኛ የጋዜጠኝነት ትምህርት ነበራቸው። ተጠርተው አዲስ አበባ መጥተው ወደ ታንዛኒያ ሄዱ። የፖለቲካና የውትድርና ትምህርትም ተማሩ። ሆኖም አብዛኛው የቡድኑ አባላት ቀድሞውንም ተመልምለው ሲላኩ ከአገር መውጫ ይሆነናል ብለው እንጂ ከልባቸው አልነበረምና ሁሉም ቆይታቸውን አልወደዱትም። ‹‹በማሰልጠኛው የነበሩት አለቆቻችን ሶስት ኦፊሰሮች እና አንድ ሃምሳ አለቃም ነበር›› የሚሉት እንግዳችን እነዚሁ አለቆቻቸው እንዳይወጡ ፓስፖርታቸውን ወስደው ማስቀመጣቸውንም ያስታውሳሉ። እንዳከሉት ልውጣም ቢሉ ማሰልጠኛው ያለው ከዳሬ ሰላም ከተማ በጣም ሩቅ በመሆኑ ስለማይቻል ተስፋ ቆርጠው ነበር ስልጠናውን እየወሰዱ የሚገኙት። ታድያ አንድ ዕለት ሰልፍ እየተማሩ ሳለ “ተጠንቀቅ! ሲባል አንዱ ጠመንጃውን ጣለው፣ እና ለጣለው ጠበንጃ ሰላምታ ስጠው ተባለ፣ አልሰጥም አለ፣ ልጁን ታድያ ወስደው እስር ቤት አስገቡት፣ እስር ቤት

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

ውስጥ እሪ ብሎ ሲጮህ ምን ሲደረግ ጓደኛችን ይነካል ብለን ረብሻ ቀሰቀስን፡፡ "መጨረሻ ላይ በነሱ ጥያቄ ኬንያ የነበሩ አምባሳደር መጡላቸውና አባብለው መርሃ ግብሩን እንዲያጠናቅቁ አደረጉ፡፡ ባልወደዱት ቆይታ ምሬት የሰሩት እንዲህ ዓይነቱ የልጅ መሰል ጨዋታ ዛሬም ሲያስታውሱት እንደሚያስቃቸው ይናገራሉ፡፡

### ራዲዮ ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ሬዲዮን እንደገና የተቀላቀሉት በ1975 በጥቅምት ወር ነበር፡፡ እናም በጣቢያው 'ካነበብነው'፣እና ሌሎች ፕሮግራሞች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በአብዛኛው የሠሩት ግን 'ከደብዳቤዎች ማህደር' በሚለው ፕሮግራም ላይ ሲሆን ይህ ፕሮግራም አድማጮች ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል የሚልኳቸውን ደብዳቤዎች ተመርኩዞ የሚሰራ እንደነበር ያወሳሉ፡፡ የሚያስተናግዳቸው ሀሳቦች ልክ እንደ አድማጮቹ የተለያዩ ሲሆኑ የማይዳሰሰው ርእስ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሳይንስ እንዲሆም ሌሎች በዛ ያሉ ዘርፎችን የሚመለከቱ ጥቄዎችም ያካተተ ነበር፡፡

‹‹ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ወደ ተለያዩ ባለሙያዎች በመሄድ እጠይቅ ነበር›› የሚሉት እንግዳችን ፕሮግራሙ ይቀርብ የነበረው በሳምንት ሁለት ቀናት እንደነበርም ያስታውሳሉ፡፡ ለፕሮግራሙ ይመደብ በነበረው 45 ደቂቃ ሲሆን ይሄም በጣም ሰፊ ዝግጅት የሚደረግበት ነበር፡፡ በየሳምንቱ ለጣቢያው የሚደርሱ በሺዎች የሚቆጠሩ ደብዳቤዎች እንደነበሩም ያነሳሉ፡፡ ‹‹እንደዛም ሆኖ እስክሪፕት ፅፎ፣ በድምፅ ቀርፆ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኤዲት አድርገን ማስረከብ ይጠበቅብን ነበር›› ሲሉም የሥራውን ሂደትና ክብደት ያወሳሉ፡፡ የሥራ ገጠመኛቸውን እንዳጫወቱን ማስታወቂያ ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ 1978/79 ዓ.ም. አካባቢ ከደብዳቤዎች ማህደር የተሰኘውን ፕሮግራም ሲያዘጋጁ አንድ ዩኒቨርሲቲን የሚተች ደብዳቤ ይመጣላቸዋል፡፡ ደብዳቤው ብቁ መምህር የለም የሚል ዓይነት ሲሆን፣ ጽሑፉን የፃፈው እንዴት እንደዚህ ያለ ሰው ዩኒቨርሲቲ ይቀጥራል ብሎ ነበር፡፡ ወቅቱም የደርግ ነበርና ኢሠፓ ከሚባል ድርጅት የርዕዮተዓለም መምሪያ ሰዎች እንዲህ ዓይነቱን ደብዳቤ ለምን አስተላለፈ ብለው ሊይዟቸው መጡ፡፡ ‹‹አለቆቼ ማስተባበያ ይሰጥበታል እንጂ እንዴት በዚህ ተጠያቂ ይሆናል› ሲሉ ተከላከሉልኝ፡፡ እናም ሁለተኛ እንዲህ ዓይነት ክስና ሂስ አያስፈልግም አሉ›› የሚሉት እንግዳችን በዚህ ዓይነት አሠራር የሚሄድ ጋዜጠኝነት በምንም ዓይነት ሊያድግ አይችልም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡


### ከጋዜጠኝነት የወጡባቸው አጋጣሚዎች

እንግዳችን ከጋዜጠኝነት ሕይወት የወጡባቸው አጋጣሚዎች አሏቸው፡፡ አንዱ ከጋዜጠኝነት ሙያቸው ጋር ተያያዥነት ያለው እና ከ1980 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ኢህአዴግ እስከ ገባበት ጊዜ ድረስ ቡናና ሻይ ልማት በሚባለው መሥሪያ ቤት ተቀጥረው በሕዝብ ግንኙነት ሙያ ያገለገሉበት ነው፡፡ ሁለተኛው አንድ ሁለት ዓመት በሌላ ሙያ ተሰማርተው የነበሩበትና ከዚሁ ለጠቅ አድርገው በትርጉምና የማማከር /ኮንሰልቴሽን/ ሥራዎች ሲሰሩ የቆዩበት ነው፡፡

### ወደ ሙያ መመለስና እስር

‹‹ከዚያ በኋላ ወደ ቀደመው ጋዜጠኝነት ሙያዬ ተመልሼ አሌፍ የሚባል መፅሔት አሌፍ በሚባል ኢንተርፕራይዝ ሥር በማቋቋም ማሳተም ጀመርን›› ይላሉ፡፡ ይህንን ድርጅት አብረዋቸው ከመሠረቱት ውስጥ አቶ ብርሃነ መዋ፣ መዓዛ ብሩ፣ ተፈሪ ዓለሙ፣ እሸቱ ጥሩነህ፣ ይገኙበት ነበር፡፡ ነገር ግን በጊዜው የነበረው መንግስት አካሄዳቸውን የወደደላቸው ባለመሆኑ ይሄም ቢሆን ለአንድ ሁለት ዓመት ያህል ብቻ ነው የዘለቀው፡፡ በዚህ የተነሳ እሳቸውና አቶ ብርሃነ ለስድስት ወራት ታስረው ቆዩ፡፡ ከስር ቢፈቱም ፍርድ ቤቱ ተጠርጥረው በተከሰሰኩበት ወንጀል ጉዳይ ነፃ ብሎ ያሰናበታቸው ከሁለት ዓመት ክርክር በኋላ እንደነበርም ያወሳሉ፡፡ ሲታተም የነበረው መጽሔት እና ጋዜጣ (ጋዜጣው ደወል የሚል ስያሜ ነበረው) ጉዳይ በዚሁ ሳቢያ ተቋረጠ፡፡

እንግዳችን ከዚህ በኋላ ወደ አሜሪካን ድምፅ ተዛውረው አንድ ሁለት ዓመት ያህል የሰሩ ሲሆን በተለያዩ የመንግስት ጫናዎችና ተፅእኖዎች የተነሳ ሳይሳካላቸው ቢቀርም የራሳቸውን ሬዲዮ ለመክፈትም ሞክረዋል፡፡ በሙያ ሕይወታቸው እጅግ ካዘኑባቸው ጊዜያቶች ቀዳሚው ይሄ ጊዜ መሆኑንምያነሳሉ፡፡ አቶ መለስካቸው እንደሚሉት በኛ አገር ባለስልጣናትና ኃላፊዎች እነሱ ብቻ ለአገር የሚያስቡ እንደሚመስላቸው የታዘቡበት ነው፡፡ ይሁንና የአንድ ባለስልጣን ያህል ወይም በበለጠ



አስተማሪዎች፣ ጠበቆች፣ ነጋዴዎችና ሌሎችም ለአገር የሚያስቡ እንዳሉ ማሰብ እንደሚያስፈልጋቸው ያስገነዝባሉ፡፡

‹‹እኔ ብዙ ጊዜ እንደገጠመኝ አንድ ዜጋ በሕግም በተፈጥሮም መብት እንዳለው የማይረዱ አሉ›› ሲሉም ለአብነት የዛሬ 20 ዓመት ግድም አዲስ ብሮድካስቲንግ ካምፓኒ (ኤቢሲ) የሚባል የራዲዮ ድርጅት ለማቋቋም ብዙ ሲሰሩ ወደ ነበረበትም ትዝታ ይመለሳሉ፡፡ ድርጅቱን እሳቸውን ጨምሮ ብዙ ሆነው በራሳቸው ገንዘብ እንዳቋቋሙትም ያስታውሳሉ፡፡ ታዲያ በወቅቱ ኤቢሲ ለተባለው ድርጅት የራዲዮ ሞገድ አልተፈቀደም ነበርና እስኪሳካ የተቀጠሩት ጋዜጠኞች እንዳይቦዝኑ ተብሎ "አዲስ ዜና" የተሰኘችውን ጋዜጣ እያዘጋጁ ቆዩ፡፡ የጋዜጣዋ ሕትመት ሁለት ዓመት ያህል ዘልቋል፡፡ ኤቢሲን ለመጀመር ከጋዜጣው ህትመት ጎን ለጎን ጋዜጤኞችን በማብቃት በጣም ተዘጋጅተዋል፡፡ አገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ውጭ አገር ድረስ ወስደው ጋዜጠኛ አሰልጥነውም ነበር፡፡ ሁኔታውን ሲያብራሩም ‹‹አዲስ አበባ፣ ናይሮቢ፣ ኖርዌ ጊምሊኮለን ስኩል ኦቭ ጆርናሊዝም ኤንድ ኮሚኒኬሽንስ አሰልጥነን፣ መሣሪያ አስገብተናል›› የሚሉት አንጋፋው ጋዜጠኛ መለስካቸው ይሄን ሁሉ ያደረጉት ከቀና ሃሳብ በመነሳት መሆኑንም ያወሳሉ፡፡ ይሄን ለማድረግ ሕጉም ይፈቅድላቸው እንደነበር ያነሳሉ፡፡ ግን ተወዳድረው ዕድሉ ለነሱ ሳይሆን ለሁለት የተወሰኑ ቡድኖች ተሰጠ፡፡

‹‹በዚያን ጊዜ ቢሰጠን ለዘርፉ እድገትም ሆነ እንደ አገር ለውጥ ለማምጣት ብዙ አስተዋፅኦ ማበርከት እንችል ነበር፤ ይህን ስል ለሌሎች ለምን ተሰጠ ማለቴ አይደለም›› የሚሉት እንግዳችን ጭራሽ ባልተፈፀመ ወንጀል፣ ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ከውጭ ያስገቧቸው ከሬዲዮ ጋር የተገናኙ የእስቱዲዮ መሣሪያዎች በሙሉም በጉምሩክ ሠራተኞችና በፖሊሶች ተቆራርጦ መወሰዱንና የት እንዳደረሱት እስከዛሬም እንደማያውቁ ይገልፃሉ፡፡ የሬዲዮ ጣቢያው ሥራ በዚህ መንገድ ሲደናቀፍ የህትመት ሥራ ለመጀመር ኩባንያው ከውጭ ያስገባው የህትመት መሳሪያም "ከዓላማው ውጭ ሄዷል" በሚል የሃሰት ክስ አስመስርቶባቸዋል፡፡ እናም ከኤቢሲው ጋር በተያያዘው ጉዳይም የሀሰት ክስ ተመስርቶባቸው ዕጣቸው ዘብጥያ መውረድ ለመሆን ተገድዷል፡፡

በእርግጥ ‹‹በኢህአዴግ ጊዜ በመታሰሬ አካላዊ ስቃይ ባይደርስብኝም መንፈሳዊ ስቃይ ደርሶብኛል፡፡ ራሱ አለአግባብ መታሰሬን እንደ አንድ ትልቅ ሥቃይ ነው የምቆጥረው››የሚሉት እንግዳችን ለእስር አዲስ እንዳይደሉም ይናገራሉ፡፡ እሳቸው እንዳጫወቱን ደርግ ከመስከረም 2 1967 ዓ.ም ጀምሮ ባወጣው ጊዜያዊ ዐዋጅ ማሰብም ጭምር ተከልክሎ ነበርና በፀረ-አብዮተኛነት ተጠርጥረው ታስረዋል፡፡ የታሰሩት ከደርግ ውጭ በማሰባቸው ነበር፡፡ ያኔ በአስተሳሰብ ከገዢው ክፍል መለየት ያስጠረጥር ነበር፣ ለአገር መሥራት ማሰብ፤ መቆርቆር በዚህ ወይም በዚያ ድርጅት ብቻ ሳይሆን በሌሎች በርካታ ኢትዮጵያውያን ዘንድም ነበር፡፡ ይሄም ያሳስር ስለነበር ነው የታሰሩት፡፡ በኢህአዴግ ግዜ ግን የታሰሩበት ምክንያቱ ትርጉሙ ለፍቺ አስቸጋሪ ነበር፡፡ በእርግጥ ሕገወጥነት በናኘበት ስርዓት እንዲህ ዓይነት አሠራር የተለመደ በመሆኑ ብዙም አላስደነቃቸውም፡፡ ‹‹ይህን ስል ግን እንዲያው ምንም ማለት አይደለም፣ ምንም መባል የለበትም፣ ዝም ብሎ የሚታለፍ ነው ማለቴ ሳይሆን መወገዝ፣ መጠየቅ ያለበት ነው›› ይሉታል፡፡ በዘመኑ እሳቸው በታሠሩበትና አሁን አዲሱ የአፍሪካ ህብረት ህንፃ በቆመበት ስፍራ በነበረው እስር ቤት (ከርቸሌ) በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞች የታሰሩበት ነበር፡፡ በቆይታቸው ከታሰሩት 98 ከመቶ የሚሆኑት እሥረኞች የፍርድ ቤትን ደጃፍ የረገጡ አለመሆናቸውን ያስታውሳሉ፡፡ ‹‹በጭካኔ፣ በግርፋት አካሉ ጎደሎ ሆነው በሕይወት ያሉ አሉ›› ሲሉ ያለፉበትን ያስታውሳሉ፡፡ መጨረሻ ላይ በኢህአዴግ ጊዜ ሁሉም ሙከራቸው ባለመሳካቱ አሁን እየሰሩ ወዳሉበት የአሜሪካን ድምፅ ተመለሱ፡፡

### ሙያዊ አተያይ

በየስርዓቱ የነበረው የጋዜጠኝነት የሙያ ጫና በእንግዳችን አተያይ በተለያየ መልኩ ይገለፃል፡፡ በዓፄ ኃይለስላሴ ዘመን በሙያው ባይሰሩም አበጥረው ያውቁታል፡፡ እንደሳቸው የጋዜጠኝነት ሙያ በአፄው ጊዜ አሁን በምናውቀው አሰራር ጋዜጠኝነት ይተገበር ነበር ለማለት ያስቸግራል፡፡ ይሁንና አንዳንድ የጋዜጠኝነት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ፣ እንዲሁም ራሳቸውን ያስተማሩና ያበቁ እንዲሁም ንቁ የነበሩ በራሳቸው ለመሥራት የሞከሩ ነበሩ፡፡ በግላቸው፣ የሚፈለገውን መረጃ ለሕዝብ ለማድረስ፣ በሕዝቡና በመንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት አፍታተው ለመግለፅ የሞከሩና የሠሩ ሰዎች እንደነበሩ መካድ ትልቅ ስህተት ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን የጋዜጠኝነት ሥራ የተመቸና ጥሩ ነበር ማለት አይደለም፣ እንኳን ያንጊዜና ዛሬም እንደዚያ ያለ ሁኔታ አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡

በመሠረቱ የጋዜጠኝነት ሥራ ነፃነት ይፈልጋል፣ ዕውቀትና ብቃት ይጠይቃል፣ የዚህ ሁሉ ዝግጅት አልነበረም፣ የጋዜጠኝነት ትምህርት ቤት አልነበረም፣ ሆን ብለው ጋዜጠኝነትን ለመማር ውጭ ከሄዱት በስተቀር አገር ውስጥ ምንም አመቺ ሁኔታ አልነበረም፣ በጋዜጠኝነት ሰዎችን ሊያንፁ የሚችሉ ተቋማትም ሆነ አሠራር አልተዘረጋም ነበር፣ በራሳቸው አነሳሽነት በማንበብ፣ ጥረት በማድረግ ብዙ ጥሩ ጥሩ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ግን ነበሩ፡፡ ለአብነት በ1968/69 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለተወሰነ ጊዜ የአብዮት መድረክ የሚባል ዐምድ ነበር፣ በዐምዱ ታዲያ የተለያየ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ስለ አገሪቱ ፖለቲካ ሁኔታ ሀሳብ ያቀርቡበት ነበር፡፡ በወቅቱ ሰው ስለአገሩም ሆነ ስለፖለቲካ የተለያየ አስተያየት ይልክ፤ ከፍተኛ የሆነ ክርክርም ይደረግ ነበር፡፡

የግል መፅሔቶችም ይወጡ ነበር፣ የተለያየ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች እንዳውም በግልፅ በሚያስታውቅ ዓይነት የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖችም አስተያየቶች ይንፀባረቁ ነበር፣‹‹በዚህ ወቅት የጋዜጣው ኮፒ በከፍተኛ ሁኔታ ይሸጥ ነበር››የሚሉት እንግዳችን ይሄን በሳቸው መነጽር ሲያዩት የሚያሳየው ነፃነት ለፕሬስ ዕድገት ምን ያህል አስፈላጊና ጠቃሚ እንደነበርም ይገልፃሉ፡፡ ደርግ ይሄን ሁኔታ ሲቀለብሰውና ሲያፍነው መልሶ ጨለማ ሆነ፡፡ እንደ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እንደነበረው አንድ ወጥ እና የመንግስት አገልጋይ ብቻ የሆነ ፕሬስ ሆነና ጋዜጣውም፣ ሬዲዮኑም፤ ቴሌቪዥኑም ዕጣ ክፍላቸው እንዲሁ አንድ አይነት አሰልቺ ዜማ እንዲያዜሙ ተገደዱ፡፡ የግል የሚባል ነገር ቀረ፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ በ1983 ኢህአዴግ ከመጣ ወዲህ ቻርተሩን ጨምሮ ያወጣቸው ህጎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የተሻለ ነገር ማሳየቱን ያወሳሉ፡፡ ሰው ነፃነትን ማጣጣም መጀመሩንም ያስታውሳሉ፡፡ የተለያዩ ጋዜጦች፣ የተለያዩ መፅሔቶች እንደአሸን መፍላታቸውንም ይጠቅሳሉ፡፡ ብዙ የተሻሻሉ ምልክቶችም መታየት ጀምረው እንደነበርም ያነሳሉ፡፡ ‹‹መቸም ባህርይ ያልሆነ አይፀናምና ኢህአዴግም ወደራሱ ማንነት ሲመለስ በራሱ መንገድ መጨቆን ጀመረ›› የሚሉት እንግዳችን ‹‹እኛን ሲያሸማቅቅና ሲያስቸግር እኔን አትወዱም ብሎ እንጂ አገር አትወዱም ብሎ እኮ አልነበረም፡፡ እንደሳቸው የሕግ የበላይነት አለመኖር፣ የዲሞክራሲ አለመኖር፣ የሰው ልጅ መሠረታዊ የሆኑ መብቶችን አለማክበር አሁንም እርምጃችንን ቀፍድዶ እንደያዘን ነው፡፡ ታሪካችንን ከዚህ አቅጣጫ አጢኖ ትክክለኛውን መንገድ መምረጡ ከውድቀትም ከፀፀትም ያድናል፡፡

### ጋዜጠኝነት፤ ጋዜጠኝነት መሰል አካሄድና መልዕክት

በአሁኑ ወቅት ብዙ ጋዜጠኛ የሚያስመስላቸው ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ከመበራከታቸው ጋር አያይዘው እንግዳችን ‹‹ማንም የሚያንጎራጉር ሁሉ ሙዚቀኛ እንደማይሆነው ሁሉ የፃፈ ሁሉ ጋዜጠኛ አይደለም›› ይላሉ፡፡ ስለ ትክክለኛውና ሕጋዊው የጋዜጠኝነት ሙያና ስለደረሰበትም ደረጃ ያብራራሉ፡፡ እንደሳቸው በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው ጋዜጠኝነት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ በትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጥ የትምህርት ቤት አካል የሆነ የትምህርት መስክ ነው፡፡ እንደማንኛውም የትምህርት መስክ ብዙ ድካም የሚሻ፣ ብዙ ጥብቅ ዲሲፕሊን የሚፈልግ፣ ትጋት የሚጠይቅ፤ ሥርዓቱም እየሰፋ፣ እያደገ የሚሄድ ትምህርትና ሙያ ነው፡፡ በመሆኑም መማር እንደሚያስፈልግ ይመክራሉ፡፡

እንደሳቸው ጋዜጠኞች ሁሉ በዚህ መስመር ብቻ መምጣት ላይኖርባቸው ይችላል፡፡ ሆኖም አሁን አገሪቷ ላለችበት "ምስቅልቅል ችግር" በዚህ መስመርና መሥፈርት ያልመጡ ጋዜጠኛ ተብዬዎች ምክንያት ስለመሆናቸው ጥናትና ምርምር፣ ግምገማና ትኩረት የተሞላበት ክትትል እንደሚፈልግ ያነሳሉ፡፡ እንደሚሉት ደግሞ "ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው" የሚባል ነገር አለና አለዐውዱ የተዘገበ ዜና ወይም ወሬ መደነጋገር፣ ውዥንብር እንደሚፈጥር ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ዋናው ነገር ግን ይሄ ሳይሆን መንግሥት እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ለመፍታት፣ ለመቆጣጠር ምን ያህል ሞክሯል፤ ሕግን ለማስከበር ምን ያህል ሄዷል የሚለው ነው፡፡ የመንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ ሕግን ማስጠበቅ ነው፡፡ አቅም አለን የሚሉ ጉልበተኞች አቅም የሌላቸውን ሰዎች እንዳይበድሉ ዜጎችን መጠበቅ ነው፡፡ መንግስት ይሄን ካላስተካከለ ጋዜጠኝነት ያድጋል ማለት እንዳው ከንቱ ምኞት ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

ጋዜጠኝነት የራሱ ደሴት የለውም፡፡ ‹‹በአንድ አገር ማንኛውንም አገሪቱን የሚገዛውና የሚያስተዳድረው ሕግና ሥርዓት ነው›› የሚሉት እንግዳችን ሌላውን የሕብረተሰብ ክፍል፣ የማሕበረሰቡ አካላት ሁሉ እንዲሠራ፣ እንዲነቃ የሚያስችለው እንዲህ ዓይነት ሥርዓት ተዘርግቶ፣ ጋዜጠኝነትም በዚህ ዐውድ ሲሠራ ብቻ ነው የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ እስከ አሁን ባየሁትና በነበርኩበት ጊዜያት ሁሉ ከፍና ዝቅ እያለ ነው ሲጓዝ የነበረው፣ አንድ መስመር አይደለም የተከተለው፣ ከኃይለሥላሴ ጊዜ ጀምሮ በነበሩት ሥርዓቶች አከታትለን ጋዜጠኝነትን ብናየው በዚህ ጊዜ ጥሩ በዚያ ጊዜ መጥፎ የምንለው የወቅት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አዳጋች ነው፣ ይላሉ፡፡ በየዘመኑ አንዴ ከፍ ሲል ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ ሲል ኖሯል፤ በአንፃሩ ጋዜጠኞቹንም ብናይ እንዲሁ ነው፣ ጋዜጠኝነት በዛሬው ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ነው፣ ትክክለኛ ትምህርትም፣ ትክክለኛ ዲስፕሊንም ያለው ቁጥሩ አናሳ ነው፣ በመታደልም ይሁን ባለመታደል ዛሬ ማንም ሰው 'ጋዜጠኛ' መሆን ይችላል፡፡

ይሄ የሚሠራው ሥራ ለሕዝብ ይጠቅማል አይጠቅምም የሚለው ሌላ ጉዳይ ሆኖ ጋዜጠኝነት ግን እሳቸው በሚያውቁት መንገድ ቢማሩት ሁልጊዜ የሚያድግና ብልሃትና ዘዴውን ደግሞ ቢያውቁት፣ እንደዚህ ያለ ዝብርቅርቅ ነገር ሊታይ አይችልም ብለው ያስባሉ፡፡ በመሆኑም ትክክለኛ ትምህርት ይፈልጋል፣ ትክክለኛ ስልጠና ይፈልጋል፣ ዲስፕሊን ይጠይቃል፣ ከፍተኛና ብርቱ ትጋት የሙያው ምርጫ ነው፡፡ ለአንድ ጋዜጠኛ ማንበብ ልምድ መሆን አለበት፡፡ እና በዛው መጠን ማንቃት እንችላለን፣ ሕብረተሰቡን ማነፅ ተግባራችን ይሆናል፣ ይህን ኃላፊነት አለመገንዘብ ጋዜጠኝነትን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰብን አገርን አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ስለዚህ በጥንቃቄና በኃላፊነት መሠራት ያለበት ሙያ ነው ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጎን ለጋዜጠኞች በየጊዜው ትክክለኛ መረጃ መስጠት፣ ብቃታቸው ከፍ እንዲል የሚያስችሉ አሠራሮችን መፍጠር፣ በዛ ውስጥ እንዲያልፉ ማድረግ፣ ጋዜጠኞቹን ወይም ጋዜጠኝነት ሥራ እንሠራለን የሚሉና ፍላጎት ያላቸው ወጣቶችን በምኞታቸው እንዲያልፉ ማገዝ ተገቢ ነው ባይ ናቸው፡፡

‹‹አንድነት ስለተፈለገ ብቻ ሳይሆን የሚመጣው ብዙ ሥራ ይፈልጋል›› የሚሉት እንግዳችን › ልዩነት እኮ የተፈጥሮም ባህሪ ነው፣ ቁምነገሩ ልዩነትን የሚፈጥሩ ነገሮች ምንድናቸው፣ ግጭትን የሚፈጥሩ ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው፣ በማለት መመርመር ነው፤ ከዚህ የሚርቅ አይመስለኝም መፍትሔው፣ ቋንቋ ችግር ይፈጥራል ብዬ አላስብም፣ የባህልና የዘውግ ልዩነትም አይመስለኝም፣ እኔ እንደሚመስለኝ ድህነት ነው፤ መነሾው የሚመስለኝ፡፡ ጥቂቶች ከሕብረተሰቡ አላግባብ ሲያተርፉ፣ ሲጠቀሙ የሚመጣ ችግር ነው፡፡

ይሄ ታዲያ ማህበራዊ ቀውስ፣ የኢኮኖሚ ቀውስ፣ የፖለቲካ ቀውስም ጭምር ያመጣል፣ እዚህ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል እስከዛሬ ልንሠራ ያልቻልነው ይህንን ነው" ሲሉ መልክታቸውን ያስተላልፋሉ፡፡ እኛም በዚሁ መልዕክት የአንጋፋውን ጋዜጠኛ መለስካቸው አመኃን የሙያና የሕይወት ተሞክሮ ያጋራንበትን ጽሑፍ ቋጨን፡፡

# የመካነ ቅርሶች ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ጉዳት መጋለጥ- ሳይቃጠል በቅጠል

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የበርካታ ዓለም አቀፍ መካነ ቅርሶች ባለቤትና መገኛ ናት። ስልጣኔን፣ ዘመናትን የተሻገሩ የአገረ መንግስት ግንባታን፣ ባህልን፣ ታሪክንና የህንፃ ግንባታ ጥበብን እንዲሁም አገር በቀል እውቀትን የያዙ የመስህብ ሃብቶች መገኛ አገር ነች። እነዚህ ሃብቶች ከትውልድ ትውልድ ተሻግረው የቀደምት ኢትዮጵያውያንን ታላቅነትና የዚያን ዘመን የኢትዮጵያን የገዘፈ ማንነት ሊመሰክሩ ህያው ሆነው ይገኛሉ።

ከአገር አልፈው የዓለም አቀፍ ቅርስ የሆኑት እነዚህ በርካታ የመስህብ ሃብቶች የያኔው ዘመን ምስክር ከመሆን ባለፈ በዛሬው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮቻችን ላይ ጉልህ አስተዋፆኦ እያበረከቱ ናቸው። በተለይ ትውልድን በሚዳሰስና በሚጨበጥ ማስረጃ ለማስተማር፣ ለአገር ገፅታ ግንባታና ለቱሪስት መስህብነት እያገለገሉ ይገኛሉ። ካላቸው ፋይዳ እኩል ግን ጥበቃና ከለላ እንደማያገኙ የሚያመላክቱ በርካታ መረጃዎች አሉ።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ዓለም አቀፍ ቅርሶች ካላቸው የላቀ ፋይዳ አንፃር በልኩ ትኩረት ሊሰጣቸው፣ ሊጠበቁ፣ አስፈላጊው እድሳት ሊደረግላቸውና ተገማች ከሆኑ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ጉዳቶች አስፈላጊውን ከለላ ሊያገኙ ይገባል። ከዚህ አኳያ በአገራችን የሚገኙ መካነ ቅርሶችም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የሚያመላክት ግልፅ የሆነ የጥናትና ምርምር ውጤት ከአንድ ቋት ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም፣ እስከ ውስንነታቸው በጥቂቱም ቢሆን አመላካች ማስረጃዎች በየጊዜው ይወጣሉ።

ከዚህ ውስጥ በአማራ ክልል በጎንደር አካባቢ የሚገኙ መካነ ቅርሶች የሚገኙበት አሁናዊ ሁኔታን የሚያሳየው መረጃ ይገኝበታል። የዝግጅት ክፍላችንም ጥቅል የኢትዮጵያ መካነ ቅርሶች ወቅታዊ ሁኔታ ባያሳይም የተወሰኑ የእይታ መንሸዋረሮችን እንደሚያስተካክል በማመን የሚከተለውን ዳሰሳ ይዞላችሁ ቀርቧል።

በጎንደር ዓለም አቀፍ መካነ ቅርስ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ያተኮረ ለባለድርሻ አካላትና ለቅርስ አስተዳደር ኮሚቴ አባላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በቅርቡ ተሰጥቷል። በወቅቱም በአካባቢው የሚገኙ መካነ ቅርሶች ለሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ አደጋዎች የሚጋለጡባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው ተጠቁሟል። አስፈላጊው የጥንቃቄ ጥበቃ እርምጃ መወሰድ እንዳለበትም ተመላክቷል።

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አየለ አናውጤ ይህንን ሃሳብ ይጋራሉ። ከትውልድ ትውልድ ተላልፈው እዚህኛው ትውልድ ላይ የደረሱት እነዚህ መተኪያ የሌላቸው ቅርሶች ከአራት ምእተ ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠሩ እንደ መሆናቸው በቆዩበት ዘመን ለተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎችም የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ መሆኑን ዶክተር አየለ ይገልጻሉ። መካነ ቅርሶቹ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት ለተለያዩ አደጋዎች መጋለጣቸውንም አመልክተዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶችን የመጠገን ልምድ አናሳ መሆኑ፣ ቅርሶች የከፋ ጉዳት ሳይደርስባቸው ለመታደግ እና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚደረው ጥረትም እንዲሁ በሚፈለገው ልክ እንዳልሆነ በመጠቆም፤ መንስኤዎችና መፍትሄዎች ላይ የጠራ ግንዛቤ መያዝ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሕይወት ኃይሉ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የበርካታ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት መሆኗን ጠቅሰው፣ በአገሪቱ የሚገኙ እነዚህ በዓይነትና በብዛት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች የኢትዮጵያውያን ማንነት መገለጫ ህያው ምስክር መሆናቸውን ያስረዳሉ። እነዚህ መተኪያ የሌላቸው፣ ከዘመን ወደ ዘመን ተሸጋግረው እዚህኛው ትውልድ ላይ የደረሱና ኢትዮጵያን ከቀሪው የዓለም ክፍል ጋር ያስተዋወቁ ቅርሶች በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት የተለያዩ አደጋዎች ተጋርጦባቸው እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በፌዴራል፣ በክልል፣ በወረዳ፣ በቅርሱ ባለቤቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት፣ በግሉ ዘርፍ ውስጥ በተሰማሩ የቅርስ አስተዳደር አማካሪ ኮሚቴ እንዲሁም ቅርሶቹ በሚገኙባቸው አካባቢ የሚኖሩ ባለድርሻ አካላት በመካነ ቅርሱ ነባራዊ ሁኔታ ጥበቃ፣ ልማትና አስተዳደር ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ በመያዝ ቅርሶቹን ከአደጋ መታደግ እንደሚያስፈልግ ሁለቱም የመንግስት አመራሮች አፅእኖት የሰጡበት ጉዳይ ነው።





### የጎንደር መካነ ቅርሶች አሁናዊ ገፅታ

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የመካነ ቅርስ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር ወይዘሮ ፀሃይ እሸቴ ፋሲል ግቢ በጎንደር ዘመነ መንግስት የተሰሩትን አብያተ መንግስታትን የያዘ መካነ ቅርስ እንደሆነ ይናገራሉ። ቅርሱ እ.ኤ.አ ከጥቅምት 22 እስከ 26 ቀን 1979 በተካሄደው የዓለም ቅርስ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ከስድስቱ የመምረጫ መስፈርቶች መካከል ሁለቱን በማሟላት ሶስተኛው የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ቅርስ ሆኖ መመዝገቡን ያስረዳሉ። ቅርሱ በጎንደር ከተማ እና ከጎንደር ከተማ ውጪ የሚገኙ ዘጠኝ መካነ ቅርሶችን የያዘ መሆኑን ይገልፃሉ።

ዓለም አቀፍ ቅርሱ በህግ የተከለለ ጥብቅ (Core Zone) እና አዋሳኝ (Buffer Zone) ዞን፣ የረዥምና የአጭር ጊዜ የአስተዳደር ዕቅድ ሰነድና የቅርሱን የዕለት ከዕለት ክትትል የሚያደርግ የአስተዳደር መዋቅር እንዲሁም የስጋት አስተዳደር ሰነድ ያለው መሆኑን የሚገልፁት ዳይሬክተሯ ፣ ይህም በሚከተሉት የአገሪቱ መንግስት ህጎች የተደገፉ መሆናቸውን ይናገራሉ። የኢትዮጵያ መንግስት በፀደቁ የዓለም አቀፍ ቅርሱ ጥበቃ አስተዳደር የህግ ማዕቀፎች (የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት እና 209/1992 አዋጅ፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት 1995 በአንቀጽ 9 (4) "በኢትዮጵያ የፀደቁ ሁሉም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ ዋና አካል ናቸው" የሚለውን ጨምሮ አንቀጽ 41 (9) "መንግስት የአገሪቱን ታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርሶች የመጠበቅ እና የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት" የሚሉትን እንደ ማስረጃ ያጣቅሳሉ።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለፃ፤ እነዚህ ማእቀፎች ቢኖሩም አሁን ላይ መካነ ቅርሶቹን ለጉዳት የሚዳርግ ስጋት ተደቅኖባቸዋል። ዋናው የስጋት ምንጭም ከሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ የሚመነጭ እንደሆነ ይገልፃሉ። ሰው ሰራሽ ስጋቶች የሚመነጩት ከልማት ጫና፣ ከእርሻ ጋር በተያያዘ፣ ከአየር ብክለት፣ ከደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ጠንካራ እና ተግባር ላይ የሚውል የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ ችግር መሆናቸውንም ያብራራሉ።

ከልማት ጫና ጋር ተያይዞ በዋናነት የተስተዋሉት በተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ምክንያት የሚፈጠር ንዝረት እና መሰነጣጠቅ፣ ቅርሱን እየተጋፋ የመጣው የከተማ መስፋፋት፣ ከእርሻ ጋር ተያይዞ ቅርሶች በሚገኙበት አካባቢ ተጠግቶ ማረስ እና የግጦሽ መሬት መስፋፋት (ሱሲንዮስ እና ጉዛራ)፣ የአየር ብክለትና በቅርሶች ላይ በየጊዜው የሚጨመሩ አዳዲስ ግንባታዎች ተገቢ ያልሆኑ እድሳቶች ናቸው። ከአስተዳደር ክፍተት ጋር ተያይዞ ከተወሰኑት መካነ ቅርሶች በስተቀር አብዛኞቹ ጥገና እና ክትትል የማይደረግላቸው ሲሆን ይህም የሚሆነው በቅንጅታዊ አሠራር ክፍተት መኖር፣ በአመዛኙ በግንዛቤ ውስንነት በሚመነጭ ቸልተኝነት ነው።

"ከተፈጥሮ ስጋቶች የተያያዙት ከዕድሜ ብዛት ከሚከሰት ብልሽት፣ መበስበስ እና መፈራረስ ናቸው" የሚሉት ወይዘሮ ፀሃይ፤ ከተፈጥሮ ስጋቶች ጋር ተያይዞ የንፋስ መሸርሸር፣ ከማይክሮ- ኦርጋኒዝም መበስበስ ጋር በተያያዘ፣ የግብረ-ህንጻዎች በድንገት መውደቅ፣ የዕጽዋት መብቀል እና በወቅቱ ያለመወገድ የሚጠቀሱ እንደሆኑ ያስረዳሉ።

### ጎንደር- የቅርስ ዘላቂ ልማት

"ፈጣን እና ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ውስጥ የቀደመው ትውልድ አሻራ እና የአሁኑ ትውልድ ህልውና የሆኑት ቅርሶች የቀደመውን ዕውቀት በመረዳት ለዘመኑ ችግር የመፍትሔ ምንጭ ናቸው" የሚሉት ዳይሬክተሯ፤ በፍጥነት እያደገ የመጣው ዘመናዊነት እና ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ለውጥ ምክንያት ቅርሶች ከአካባቢያቸው ተለይተው የሚኖሩ ስላልሆኑ ለሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ይናገራሉ።

በመሆኑም የቅርሱን እሴት እና ከቅርሱ ወሰን ውጪ ያለውን አቅራቢያ ቦታ ከቅርሱ ጋር በማይጋጭ ሁኔታ በማልማት ቅርሶችን ለኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ በማዋል የአካባቢውን ህብረተሰብ ኑሮ ማሻሻል የቅርስ አስተዳደር ሥርዓቱ ዓላማ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

መካነ ቅርሶችን የሚጎዱት ነገሮች በአብዛኛው የሚነሱት ከቅርሱ ወሰን ውጪ በመሆኑ የልማት እንቅስቃሴዎችን ታሳቢ በማድረግ የቅርሱን ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን የሚያነሱት ወይዘሮ ፀሃይ፤ የቅርስ ቦታዎች የሚገኙት በህብረተሰብ መካከል በመሆኑ የቅርሶች ዘላቂ ደህንነት የሚረጋገጠው የአካባቢው ህዝብ በሚኖረው ተሳትፎና ተጠቃሚነት ልክ እንደሆነ ይገልፃሉ። በመሆኑም ስለቅርሶች እሴት እና ፋይዳ በቂ ግንዛቤ ያለው ህብረተሰብ በቅርሶች ጥበቃ እና ልማት ላይ ጉልህ ሚና አለው ይላሉ። በተቃራኒው ስለቅርሶች ፋይዳ በቂ ግንዛቤ የሌለው ህብረተሰብ ቅርሶችን ከመጠበቅ ይልቅ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይናገራሉ። ስለሆነም የአካባቢ ህብረተሰብ በሚኖረው የቅርስ ግንዛቤ ልክ ለቅርሱ ዘላቂ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ቀጣይነት ያለው ትምህርትና ስልጠና ያስፈልጋል ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ።

### ማህበረሰብ - አቀፍ ቱሪዝም ለቅርስ ጥበቃ

የመካነ ቅርስ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር ወይዘሮ ፀሃይ፤ የቅርስ ልማት የአብዛኛውን የህብረተሰብ ፍላጎትን እና ተጠቃሚነት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ይላሉ። ማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝም በቅርሱ አካባቢ የሚኖሩ እና የቅርሱን እሴቶች የራሳቸው የማንነት መገለጫ እና ኩራት እንደሆነ የሚያምኑ እና የቅርሱን አስተዳደር እና ጥበቃ ዓላማ እና ግብ በሚጋሩ የአካባቢ ህብረተሰብ ተሳትፎ የሚመራ የቱሪዝም ዘርፍ እንደሆነ ያመላክታሉ። ይህንን ተግባራዊ ማድረግም ውጤታማ እንደሚያደርግ ይገልፃሉ።

### የቅንጅታዊ አሰራር አስፈላጊነት

ዳይሬክተሯ በመጨረሻ ባነሱት ሃሳብ "በአገራችን እያደገ የመጣው የልማት እና የከተሜነት ፍላጎት በቅርሶች አካባቢ የሚካሄድ የልማት ስራ እንዲጨምር አድርጓል" በማለት እነዚህን የልማት ስራዎች ከቅርሶች ደህንነት ጋር በማጣጣም ለአገሪቱ የተሟላ እድገትና ቀጣይ ልማት የሚኖራቸውን ሚና ማሳደግ ተገቢ እንደሚሆን ይጠቁማሉ። በቅርሶች አካባቢ የሚካሄዱ የልማት ስራዎች በተለያዩ አካላት ባለቤትነት የሚከናወኑት በመሆኑ ለቅርሶች ደህንነት ስጋት ስለሆኑ ቅንጅታዊ አሰራር እንደሚያስፈልግም ያሳስባሉ። በመሆኑም ስለቅርሶች ጉዳይ በህግ ኃላፊነት የተሰጠው የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን በቅርሶች አካባቢ የሚካሄዱትን የልማት ስራዎች ከሚመሩት አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ዘለቄታዊ ልማትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው በዚያ አግባብ እንደሚከናወን ገልፀዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ወታደሩ፣ ግዛት አስተዳዳሪው እና ዲፕሎማቱ

**ዋስልኝ አየለ**

የመጋቢት ወር የመጀመሪያ ሳምንታት ታሪኮችን እያስታወስን ነው፡፡ ባለፈው ሳምንት ደጃዝማች ዑመር ሰመተርን አይተናል፡፡ የዚህ ሳምንት ክስተቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በጦር አዋቂነት፣ በአስተዳዳሪነት፣ በዲፕሎማትነትና በታሪክ ፀሐፊነት፣ በአትሌትነት እና በብሔር ፖለቲካ አቀንቃኝነት የሚታወቁ የተለያዩ ሰዎች ናቸው፡፡

ከ77 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 11 ቀን 1938 ዓ.ም በተለምዶ ‹‹የ60ዎቹ ትውልድ›› እየተባለ በሚጠራው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ የነበረው የብሔር ፖለቲካ አቀንቃኙ ዋለልኝ መኮንን ተወለደ፡፡

ከ51 ዓመታት በፊት በዚሁ ሳምንት መጋቢት 12 ቀን በአትሌትነት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት አቀንቃኝነት ጭምር የምትታወቀውና የምክትል ኮሚሽነርነት ማዕረግ የተሰጣት አትሌት ደራርቱ ቱሉ ተወለደች፡፡

በዚሁ ሳምንት የነበረ ሌላ የመወለድ ዜና እንጨምር፡፡ ከ124 ዓመታት በፊት መጋቢት 17 ቀን 1891 ዓ.ም መምህር፣ የሕግ ባለሙያ፣ ጋዜጠኛ፣ የታሪክ ጸሐፊ፣ ፖለቲከኛ፣ የሐይማኖት ሊቅ፣ ደራሲ እና ተርጓሚ የነበሩት ሁለገቡ ባለሙያ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ ተወለዱ፡፡

ራስ መኮንን እና ራስ ዳርጌ ደግሞ በዚህ ሳምንት ያረፉ ናቸው፡፡ የሁለታቸውን ታሪክ ዘርዘር አድርገን እናያለን፡፡ ከራስ መኮንን እንጀምር፡፡

የሸዋ ንጉሥ የነበሩት የንጉሥ ሳህለሥላሴ የልጅ ልጅ ናቸው፡፡ የንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ የአክስት ልጅ ናቸው፡፡ እኚህ ሰው የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አባት ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ናቸው፡፡ ራስ መኮንን ወልደሚካኤል በዚህ ሳምንት ይታወሳሉ፡፡ ያረፉት ከ117 ዓመታት በፊት መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም ነው፡፡



ራስ መኮንን ወልደሚካኤል

ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የተወለዱት ግንቦት 1 ቀን 1844 ዓ.ም በሸዋ ግዛተ አፄ፣ ጎላ ወረዳ፣ ደረፎ ማርያም በሚባል ሥፍራ ነው፡፡ ገና በወጣትነታቸው ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ሄደው ከአጎታቸው ልጅ ከንጉሥ ምኒልክ (በኋላ ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ) ጋር ተዋውቀው ቤተሰባዊና ዝምድናቸውን አጸኑ፡፡

በፀባያቸው ታጋሽና አስተዋይ እንደነበሩ የሚነገርላቸው ልዑል ራስ መኮንን ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ጠንካራ ወዳጆች በመሆን እንደ አባትና ልጅ ይተያዩ ጀመር፡፡ የሐረርጌን ግዛት በሚገባ በማስተዳደር ለንጉሥ ምኒልክ አገር የማቅናት ተግባር ብርቱ አጋዥ ሆኑ፡፡ ከቤተ መንግሥት ባለሟልነት ተነስተው በዘመኑ ከንጉሥ በመቀጠል ከፍተኛ ለሆነው የ‹‹ራስ›› ማዕረግም በቁ፡፡

ልዑል ራስ መኮንን የአጼ ምኒልክ ተወካይ በመሆን ሁለት ጊዜ ወደ አውሮፓ አገራት ተጉዘዋል። ወደ ኢጣሊያ በሄዱ ጊዜም የኢጣሊያ ጋዜጦች የውጫሌ ውልን ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ጥገኝነት ስር እንዳለች አድርገው የሚጽፉትን ጽሑፍ በመመልከታቸው ራስ መኮንን ተቃውሟቸውን ለኢጣሊያ መንግሥት ከነገሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የውሉን መበላሸት ለአጼ ምኒልክም አሳውቀዋል።

የውጫሌ ውል ያስከተለው የትርጉም ለውጥ መፍትሄው ጦርነት ሲሆንም ልዑል ራስ መኮንን ሰራዊታቸውን ይዘው ከአምባላጌ እስከ አድዋ በተደረጉት ውጊያዎች ላይ በመሳተፍ ታሪክ የማይዘነጋው ታላቅ ጀግንነታቸውን አስመስክረዋል፡፡ ልዑል ራስ መኮንን ከቤተ መንግሥት ባለሟልነት ጀምረው በወታደርነት፣ በጦር መሪነት፣ በግዛት አስተዳዳሪነትና በዲፕሎማትነት በፈጸሟቸው አኩሪ ተግባራት ምክንያት ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የዙፋናቸው ወራሽ እንደሚያደርጓቸውም ይወራ ነበር፡፡

ነገር ግን አጼ ምኒልክ ያሰቡት ሳይሆን ቀረና ልዑል ራስ መኮንን መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ሞታቸው በንጉሰ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት (አዲስ አበባ) በተሰማ ጊዜም ከፍተኛ ሀዘን ሆነ፡፡ ንጉሥ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክም አምርረው አለቀሱ፡፡ በወቅቱም ይህንን የተመለከቱ ሰዎች እንዲህ ብለው ገጠሙ ...

‹‹ዋ አጤ ምኒልክ እግዚአብሔር ያጥናዎ፣
በየበሩ ቋሚ ከላካይ ሞተብዎ፡፡
ሲታሰር አየነው ብረቱ ሲመታ፣
ምን ዋስ አገኘና ሐረርጌ ተፈታ፡፡
ጃንሆይ ምኒልክ ጠጉራቸው ሳሳና በራ ገለጣቸው፣
እንግዲህ ንጉሡ ምን ራስ አላቸው፡፡››

ከአልቃሾቹ መካከል አንደኛው ደግሞ የልዑል ራስ መኮንንን ደግነት ለማስታወስ እንዲህ ብሎ ሙሾ አወረደ ...

«ስልከኛው ሲያረዳ ነገር ተሳሳተው፣
መኮንን አይደለም ድሀ ነው የሞተው፡፡»
ተብሎላቸዋል፡፡

## በአጼ ቴዎድሮስ የተፈሩት ራስ ዳርጌ

የንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ አጎት የሆኑትና በጀግንነታቸው ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን ጭምር ያስጨነቁትና ያስደነቁት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ያረፉት ከ123 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 15 ቀን 1892 ዓ.ም ነበር፡፡

ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ የሸዋው ንጉሥ የንጉሥ ሳህለሥላሴ ወሰን ሰገድ ልጅ ናቸው፡፡ ራስ ዳርጌ የደጃዝማች አስፋው፣ የደጃዝማች ደስታ፣ የፊታውራሪ ሸዋረገድ፣ የወይዘሮ ትሰሜ፣ የወይዘሮ አስካለ፣ የወይዘሮ ፀሐየወርቅ እና የልጅ ጉግሳ አባት ናቸው፡፡ ወይዘሮ ትሰሜ ዳርጌ የልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ እናት ናቸው፡፡

ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ የንጉሥ ኃይለመለኮት ሳህለሥላሴ (የንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ አባት ማለት ነው) ወንድም ናቸው፡፡ በ1822 ዓ.ም ሸዋ ውስጥ የተወለዱት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ፣ የልጅነት ጊዜያቸውን በአንኮበርና በአንጎለላ አሳልፈው ወደ ጎንደር ተጉዘው በነበሩበት ወቅት በሰላይነት ተጠርጥረው ታስረው ነበር።

ይሁን እንጂ ራስ ዳርጌ ንፁህነታቸው ታውቆ ነፃ ከወጡ በኋላ በመልካም ጠባያቸውና በጦር ሜዳ ጀግንነታቸው በንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ተወዳጅነትን አተረፉ፡፡ በዚህም ምክንያት ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ራስ ዳርጌን ‹‹ዳሩ››፣ ‹‹ዳርዬ›› እያሉ ይጠሯቸው ነበር፡፡



የርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ጀግንነት ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስን ጭምር ያስጨነቀ ነበር፡፡ በንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ጊዜ ሸዋን ይገዙ የነበሩት መርዕድ አዝማች ኃይሌ ንጉሰ ነገሥቱን በመክዳት ተጠርጥረው ታስረው ነበር፡፡

ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስም አቤቶ ዳርጌን የሸዋ ገዢ አድርገው እንደሾሙ ተናገሩ፤ ነገር ግን ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ የራስ ዳርጌን የጦር ሰፈር ሲመለከቱት በጣም የደመቀና የተደራጀ ስለነበር በጣም ተጨነቁ፡፡ ንጉሰ ነገሥቱም አቤቶ ዳርጌን አስጠርተው ‹‹ዳሩዬ ፈራሁህ! በጥንድ ጦር የሚስተውን ኃይሌን ሽሬ በነጠላ ጦር ደርበህ ሁለት ሰው የምትገለውን አንተን በሸዋ ላይ አልሾምም›› ብለው በግልጽ ነገሯቸው፡፡ ራስ ዳርጌም የመከፋትና የቅሬታ ምልክት ሳያሳዩና ሳይከፉ ‹‹እሺ›› ብለው ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስን በትህትና እጅ ነሱ፡፡

ልጅ ምኒልክ (በኋላ ንጉሥ ምኒልክ፣ ከዚያም ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ) ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ በገቡና በአባታቸው ዙፋን በተቀመጡ ጊዜም፣ ራስ ዳርጌ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው ከምኒልክ ጋር ተገናኙ፡፡ ምኒልክም ሸዋ ገብተው በአባቶቻቸው አልጋ ተተክተው የሸዋ ንጉሥ ሆነው ነበርና ራስ ዳርጌ እንደመጡ ‹‹እርስዎ ቀጥታ የንጉሥ ሳህለሥላሴ ልጅ ስለሆኑ ንጉሥነቴን ልተውልዎ›› ብለው ጠየቋቸው፡፡

ራስ ዳርጌም ‹‹አይሆንም! አባታችን ሳህለሥላሴ አልጋቸውን አውርሰው የሞቱት በቀጥታ ለአንተ አባት ለንጉሥ ኃይለመለኮት ነው፤ አሁንም የነጋሲነት መስመሩ በዚያው ባንተ በኩል ነው መቀጠል ያለበት›› ብለው ንግሥናውን እንደማይፈልጉ ተናገሩ፡፡ ከዚያ በኋላም ራስ ዳርጌና ንጉሰ ነገሥት ምኒልክ እንደአባትና ልጅ ሆነው ከ30 ዓመታት በላይ ዓመታት ኖሩ፡፡

ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ የተለያዩ አካባቢዎችን በማቅናትና በማስተዳደር ስራ ውስጥ የላቀ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ከእነዚህ አካባቢዎች መካከል አርሲ፣ ሰላሌ እና አካባቢው ይጠቀሳሉ፡፡ ንጉሰ ነገሥት አጤ ዮሐንስ 4ኛ እና ንጉሥ ምኒልክ በተቀያየሙ ጊዜም አስታራቂ ሽማግሌ ሆነው ያገለገሉት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ነበሩ፡፡ ንጉሰ ነገሥት አጤ ዮሐንስ 4ኛ እና ንጉሥ ምኒልክ ደብዳቤ የሚፃፃፉት በርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ በኩል ነበር፡፡ ደጃዝማች መሸሻ ሰይፉ በሸፈቱ ጊዜም ተቆጭው፣ አስማሚውና መካሪው ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ነበሩ፡፡

በዓድዋ ጦርነት ወቅትም ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ለጦርነቱ ወደ ዓድዋ በተጓዙበት ወቅት የንጉሰ ነገሥቱን ቦታ ተክተው ዙፋን የጠበቁትና አገር ያስተዳደሩት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ነበሩ፡፡

በመልካም ጠባያቸው፣ በታማኝነታቸው፣ በበጎ አሳቢነታቸውና በጦር ጀግንነታቸው የሚታወቁት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ መጋቢት 15 ቀን 1892 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ስርዓተ ቀብራቸውም በደብረሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል፡፡

ከላይ ያየናቸው ሁለቱ ራሶች (ራስ መኮንን እና ራስ ዳርጌ) ሁለቱም የዚህ ሳምንት ተዘካሪ ናቸው፡፡ እንደመገጣጠም ሆኖ ሁለቱም የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ ሁለቱም በአንድ ወር ውስጥ ለዚያውም በአንድ ሳምንት ውስጥ ነው ያረፉት፡፡

ለመረጃዎቹ Marcus, Menelik II, መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ዕለታዊ የታሪክ ድርጊት እና የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ መጻሕፍትን እንዲሁም የተለያዩ ድረ ገጾችን በዋቢነት ተጠቅመናል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ‹‹የከተማው መናኝ››

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ገዳም የገባን ፈጣሪው እንጂ ማን ያየዋል? ይህ መናኝ ግን ከሁሉም የተለየ ነበር። ከሰውም ከፈጣሪውም ያልተሸሸገ የእራሱን የሙዚቃ ገዳም አበጅቶ የመነነ ታላቅ ጥበበኛ ጭምር ነበር። በራሱ ገዳም ውስጥ ቁጭ ብሎ ሙዚቃን እየሰራ ብቻ አልነበረም። ሙሉ ሕይወቱን ለሙዚቃ ሰውቶ እርሱ እንደ ሻማ እየቀለጠ ሙዚቃን እንደ ጧፍ ሲያበራ ኖሯል፡፡ ሙዚቃ በእሱ ላይ ስር አብቅላ እንድትወጣ እራሱን አፈርና ውሃ አድርጎ እየሞተ ሕይወት ዘራባት። ከእርሱ በላይ የበቀለችው ሙዚቃም ጣፋጭ የወይን ግንዱ ስሮች በአፍቃሪዎቿ ልብ ውስጥ ተሰድረው ይኖራሉ፡፡ የእውነትም ለሙዚቃ መኖር ማለት እንዲህ ነው፡፡

ይህ የታላቁ የሙዚቃ አቀናባሪ ኤልያስ መልካን ሕይወት በትክክል የሚገልፅ ነው። ኤልያስ መልካ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ አቀናባሪ ብቻ ሳይሆን የዜማና ግጥም ደራሲ ጭምር የነበረ ሁለገብ ሙዚቀኛ ነበር። አንድ ብሎ የሚጀምረው የሙዚቃ ሕይወቱ ያለምንም ስስት 400 ያህል የሙዚቃ ስራዎችን አበርክቷል። በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ከሮሐ ባንድ በኋላ በ1980ዎቹ አጋማሽ ገደማ ቀዝቀዝ ብሎ በነበረውን ደብዛዛ ጊዜ ኤልያስ መልካ እንደ ድንገት ብቅ ብሎ ደማቅና ብሩህ አድርጎታል፡፡ ስሜት ቀስቃሽ በሆኑ የሙዚቃ ስራዎቹ እንደ አበባ የፈካ የሙዚቃ ዓለምን በኢትዮጵያ የሙዚቃ ሰገነት ላይ አኑሯል። ከ1990ዎቹ ወዲህ በተሰሩ አብዛኛዎቹ የሙዚቃ ስራዎች ውስጥ ከበስተጀርባቸው ኤልያስ መልካ አይታጣም። በሰራቸው ሙዚቃዎች ፍቅር እየተነደፈ 'ህይወትን መስጠት ቢቻልና ምን ነበር በሰጠሁት' እያለ በቁጭት የሚንገበገብለት አድናቂውም እጅግ በጣም ብዙ ነው። ከጀሮው የገቡትን ስራዎቹን በልቡ ያጣጣመ ሁሉ በአንደበቱ ይህንን ቢል አይገርም። እሱም የእዮብ መኮንን በሆነው ድንቅ ስራው ውስጥ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር።

ነገን ላየው እጓጓለሁ
በል ሂድ ዛሬ ጠግቤያለሁ
ከንግዲህ መቼም ላትመጣ
ደህና ሁን በል ሌላ መጣ

እናም አልቀረም ከእሩቁ የታየው ያ ሌላ መጣና ወሰደው። በዚህ ሰዓት ከአፈር በታች ቢሆንም ከመቃብር በላይ ውብ አድርጎ የሰራውን የሙዚቃ መንደር ትውልድ በአይነ ህሊና እየተመለከተ መልከ ብዙ የሆነው የኤልያስ መልካን ህይወትና ስራዎቹን ሲያስታውስ ይኖራል፡፡

ኤልያስ መልካ ተወልዶ ያደገው የብዙ አርቲስቶች መፍለቂያ ከሆነችው የአዲስ አበባዋ አዲስ ከተማ፣ አብነት አካባቢ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃት ትምህርቱን በኃይሉ ተስፋዬ ትምህርት ቤት፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በከፍተኛ ሰባት ትምህርት ቤት ተከታትሏል። ትምህርት ቤት በነበረበት ወቅትም ጎበዝና ታታሪ ተማሪ እንደነበር የቅርብ ወዳጆቹ ይናገራሉ። በዚያን ጊዜ ጎበዝ ተማሪ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ነገሮች የተካነ ነውና ጎበዝ የእግር ኳስ ተጫዋችም ጭምር ነበር። የእግር ኳስ ችሎታውን የተመለከቱ ጓደኞቹም 'ትንሹ ማራዶና' ሲሉ ይጠሩት ነበር። በልጅነቱም የራሱን ክራርና ጊታር እያበጀ የሙዚቃ ጥሙን ለማርካት ብዙ ይታገል እንደነበር በሕይወት ታሪኩ ተፅፏል።

በኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ዘመን የማይፍቀውን አሻራ ማኖር የቻለው የዚህ ሰው ስም ለሙዚቃ አፍቃሪዎች እንግዳ አይደለም፡፡ እንዲያው በጨዋታ መሃል ድንገት ስለ ኤልያስ መልካ ሲነሳ 'እውነት ስለ እሱ አውቃለሁ ብሎ ብዙ ማውራት ባህርን በዋና አቋርጣለሁ እንደማለት ነው' ቢባል ማጋነን አይሆንም። በእርግጥም የዚህን ታላቅ ከያኒ ከስራዎቹ በስተጀርባ ያለው ረቂቅ ማንነቱና የተለየ የሕይወት ፍልስፍናው ይህን ለማመን ያስገድዳል። ረጋ፣ ሰከን ብሎ ከርቱእ አንደበቱ ከሚያወጣቸው ቃላት ባሻገር፣ ከፊቱ ላይ የሚታየውን ድምጽ አልባ ጥልቅ ስሜቶቹን ገልጾ የሚችል አይኖርም። ኤልያስ ወደ ሙዚቃው ዓለም ከመግባቱ በፊት የመንፈሳዊው ዓለም የመዝሙር አቀናባሪ ነበር። እድገቱም በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደነበረ ይታወቃል። ነገር ግን ከጊዜያት በኋላ የሙዚቃ ድምጽ በልቡ ማቃጨል ጀመረና መንገዱን ቀይሮ ዛሬ ወደምንመለከታትና ወደሰራት ወደዚህች ጥበባዊ የሙዚቃ መንደር ጎራ አለ። የመንፈሳዊውን ዓለም ስራ ባይጠላውም እውነተኛውና በህይወቱ የተጠራበት ትክክለኛው ቦታ ይህችው መንደር ስለመሆኗ እራሱ ተናግሯል። በተገኘበት ስፍራ ሁሉ ብቁ ሆኖ የሚታይ፣ የዳበረ ልምድና ክህሎት እንዲሁም ሁለገብ እውቀት ያለው የበሳል አዕምሮ ባለቤትና ወጣ ያለ የአኗኗር ዘይቤን የሚከተል ሰው ነበር። ከምንም በላይ ለተሰጠን ነገር መስጠት አለብን የሚልም ትልቅ የህይወት ፍልስፍና ነበረው። ወደ ሙዚቃው የገባው ሙዚቃን እንደ ውሃ ለተጠማቸው ነብሱ እንጂ ለእንጀራው አልነበረም። ወደ ሙዚቃው ዓለም ከገባ በኋላ ከአፍሮ ሳውንድ፣ ከዜማ ላስታስ፣ ከደመራና ከሌሎች ባንዶች ጋር እሱን እንደመመልከት የሚያስደስት ነገር አልነበረም። ከመድረክ ላይ ሊድ ጊታሩን ይዞ ከባንዶቹ ጋር የሚፈጥረው የተለየ ውህደት የሙዚቃን ግሩም ቃና ያሳያል። ሙዚቃን በልምድ ብቻ ሳይሆን በእውቀትም ጭምር እንዲኖራት ያደረጉትን ልዩ ልዩ ክህሎቶችን 1987ዓ/ም ወደ ያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት በመግባት ከውጭው ዓለም የሙዚቃ መሳሪያዎች በቼሎና በፒያኖ እንዲሁም ከአገር ውስጥ የባህል መሳሪያዎች ደግሞ በክራር ተምሮ ለመመረቅ ችሏል።

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ውስጥ የኤልያስ መልካ አሻራ እጅግ ግዙፍ ነው። በአልበም ደረጃ ብቻ 30 የተለያዩ አልበሞችን አቀናብሯል። ሙዚቃን ከማቀናበርም ባለፈ በዘመናዊው ሙዚቃ ውስጥ ስማቸው ገኖ መውጣት የቻሉ በርካታ ሙዚቀኞችን በብቃት እንዲሻገሩ ገርቶ አቅንቷቸዋል። በሙዚቃ ውስጥ የወለዳቸው አባታቸው ነውም ለማለት ያስደፍራል። ከእነዚህ መሃከል ሚኪያ በኃይሉ፣ እዮብ መኮንንን፣ ጎሳዬ ተስፋዬ፣ ኃይሌ ሩት፣ አረጋኸኝ ወራሽ፣ ኩኩ ሰብስቤ፣ ትዕግስት በቀለ፣ ማህሌት ገብረ ጊዮርጊስ እና ጌቴ አንለይ ሁሉም የኤልያስ መልካን የሙዚቃ ጸበል ተጎንጭተዋል። ኤልያስ በሚሰራቸው ስራዎች ሁሉ ሙዚቃ ስጋና ደም ለብሶ በአካል የተገለጠ እስኪመስለን ከፊታችን እንድናይ ካደረገባቸው በርካታ አልበሞች ውስጥ አንደኛው የቴዲ አፍሮ 'አቦጊዳ' የተሰኘው አልበም ነው። ማራኪ በሆነው ድምጽ ላይ፣ በተዋጣለት የግጥምና ዜማ ውህደት የቀረበውን አልበም ግሩምና ድንቅ አድርጎ በማቀናበር የብዙዎችን የሙዚቃ ጥም አርክቷል።

በተወዳጁ የሙዚቃ ሰው የሕይወት ታሪክ ላይ የሚያውጠነጥን አንድ መጽሀፍ ከዓመታት በፊት ለንባብ የበቃ ሲሆን የዚህ መጽሀፍ ርዕስም 'የከተማው መናኝ' ይሰኛል። መጽሀፉ ገበያ ላይ ከዋለ በኋላ በአጭር ጊዜያት ውስጥ ተወዳጅና ተፈላጊ ለመሆን ችሏል። ምክንያቱ ደግሞ ስለ እርሱ የሰማ ሁሉ የእርሱን የህይወት መንገድ ለማወቅ ይጓጓ ስለነበር ነው። ኤልያስ እልም ካለው የከተማ ፎቆች ጫካ ውስጥ ገብቶ የእውነትም መንኖ ነበር። እሱን የሚፈልግ ሰው ሊያገኘው የሚችለው ከከተማው ጎዳናዎች አልያም ሆቴሎች ውስጥ አልነበረም። እሱ ከሁሉም ነገሮች እርቆ እራሱን በሙዚቃ ውስጥ በመደበቅ የነብሱን ጥሪ ሲኖር ነበር።

ኤልያስ መልካ በስራዎቻቸው ላይ ነብስን ዘርቶ ያበቀላቸው ብዙ ድምጻዊያን ቢኖሩም ከእነዚህ መሃከል ሁሌም በልዩነት የሚነሳ አንድ ድምጻዊ አለ። ኤልያስ መልካ ብለን መቼም እዮብ መኮንን አንዘነጋውም። የዚህ ትልቁ ሚስጥር ደግሞ ኤልያስ መልካ እዮብን እንደራሱ አድርጎ በመቅረጹ በትክክልም የእርሱን መንገድ መጓዝና ማየት የቻለ ሰው በመሆኑ ነው። ለዚህም በእዮብ መኮንን ሙዚቃዎች ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ግጥምና ዜማዎች የኤልያስ መልካ ውስጣዊ አሻራዎች ናቸው። ኤልያስ እራሱን በእዮብ ውስጥ ገንብቷል፣ እንዲሁም ደግሞ እዮብ በኤልያስ ውስጥ ነበር። በጣም ተወዳጅ ከሆኑት ከእዮብ ሙዚቃዎች ከሶስት ስራዎች በስተቀር ሁሉም የኤልያስ መልካ ስራዎች ናቸው። የሁለቱም ማንነት እጅጉን የተዋሃደ ስለነበር ከስራ ውጭ የነበራቸው ቀረቤታም የተለየ ነበር። ሁለቱም ግን እንደ ወይን እንደጣፈጡ ሳይጠገቡ መሄዳቸው ልብን የሚሰብር ነበር።

ቅጣትና ምህረት ዛሬ ሰው ለያዩ
አንዱን ከፍለው አንዱን አለፉ እንዳላዩ

የኤልያስ አሻራ ካረፈባቸው የእዮብ መኮንን ስራዎች መሃከል ዘመን ተሻጋሪ ነው፡፡ እንዳጠፋሽ፣ ደብዝዘሽ፣ የቋንቋ ፈላስፋ፣ ነገን ላየው, ረከዳ፣ ማን እንደቃል፣ የምድር ድርሻዬ፣ ይዘባርቃሉ እና ሌሎች በርካታ ስራዎችም ይገኛሉ።

ይህ ታላቅ የሙዚቃ ሰው ገና በወጣትነቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ አጃኢብ የሚያሰኙ ወደርየለሽ ስራዎችን ቢሰራም የዛኑ ያህል ሽልማቶችን አግኝቷል ለማለት ግን ይቸግራል። በጥቂቱም ቢሆን ግን በተለያዩ ጊዜያት እውቅናና ሽልማቶች ተበርክተውለታል። ስራ የማይታክተው ብርቱም ነበርና ህይወቱ እስካለፈበት ጊዜ ድረስ በፋና የድምፃውያን ተሰጥኦ ውድድር ላይ በዳኝነት ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ መናኙ የሙዚቃ ሰው ኤልያስ መልካ ከሙዚቃ የተሰወረ ምንም ህይወት አልነበረውም። ከሙዚቃ አስተርፎ ለራሱ ያኖራት ሽርፍራፊ እድሜም እንኳን አልነበረችውም። የቱንም ያህል ሙዚቃን የሚወድ ሰው ቢሆን ይህን ያህል እራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው አለ ለማለት የሚከብድ ቢሆንም፤ ከሰገነቱ በላይ፣ ከምናየው ጥግ ያለውን የእርሱን ሕይወትና የሙዚቃ ፍቅር መመስከር የሚችለው ከመንደሩ ሆኖ እውነታውን መመልከት የቻለ ብቻ ነው። ለዚህ መናኝ ከሙዚቃ ያለፈ ሕይወት አልነበረውምና ትዳር እንኳን አልመሰረተም ነበር። ለተሰጠው ታላቅ ጸጋ እንደተሰጠ የኖረው ኤልያስ መልካ፣ ከሙዚቃ መሳሪያው ፊት ለፊት ከምትገኘው፣ መንኖ ከተቀመጠባት ወንበር አብዝቶ ከማዘውተሩ የተነሳ ለኩላሊት ህመም ተዳርጎ ነበር። በህክምና እየተረዳ ቢቆይም ስር የሰደደው ህመሙ አይሎ ማንም ሊረታው ያልቻለውን የሙዚቃ ፍቅሩን ሞት ረታው። እናም መስከረም 24 ቀን 2012 ዓ.ም በ42 ዓመቱ ይህችን ምድር ተሰናብቶ ሄደ። ኤልያስ መልካ ለሙዚቃ መጣ፣ ለሙዚቃ ኖሮ፣ ለሙዚቃም ሞተ።



ኤልያስ መልካ

# ዓለም አቀፍ



## በቱኒዚያ ጠረፍ የስደተኞች ጀልባ የመስመጥ አደጋን ተከትሉ 34 ሰዎች ደብዛቸው ጠፍቷል

ከሰሐራ በታች ካሉ አገራት እንደሆኑ የተገመቱ ስደተኞች የተሳፈሩባት ጀልባ ሰምጣ የ34 ሰዎች ደብዛ ጠፍቷል። ከስደተኞቹ መሀል ልጆችና ጨቅላ ሕጻናት ይገኙበታል። የስደተኞች ጀልባ ሲሰጥም ይህ በሁለት ቀናት ውስጥ አምስተኛው ጀልባ መሆኑ ነው።

ለጊዜው ሰባት ሰዎች መሞታቸው የተረጋገጠ ሲሆን በሁለት ቀናት 67 ሰዎች በድምሩ ደብዛቸው ጠፍቷል። የቱኒዚያ ባለሥልጣናት እንደሚገምቱት ጀልባዎቹ ይጓዙ የነበረው ወደ ጣሊያን ነበር። ባለፉት ሁለት ቀናት ብቻ የቱኒዚያ የጠረፍ ጠባቂዎች 56 ጀልባዎች ወደ ጣሊያን ሊያመሩ ሲሉ በቁጥጥር ሥር አውለናቸዋል ብለዋል።

የድንበር ጠባቂዎቹ ኃላፊ ሆሳም ጀባብሊ ለቢቢሲ እንደተናገሩት ሰሞኑን ብቻ ሦስት ሺህ የሚሆኑ ስደተኞች ወደ ጣሊያን ሊሳፈሩ ሲሉ በቁጥጥር ሥር ውለዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቱኒዚያ ወደ አውሮፓ ለሚያቀኑ ስደተኞች ዋነኛ መነሻ ወደብ ሆናለች። የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው መረጃ በዚህ ዓመት ወደ ጣሊያን ከተጓዙ ስደተኞች 12ሺህ የሚሆኑት መነሻቸው ቱኒዚያ ነበር። ይህ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ12 እጥፍ ብልጫ አለው።

ባለፈው ወር የቱኒዚያ ፕሬዚዳንት ካይስ ሰኢድ ከሰሐራ በታች የሚመጡ ጥቁር አፍሪካዊያን በአገራቸው ወንጀል እያለማመዱ እንደሆነና ለአረብ ለቱኒዝያ ጥቁሮች አደጋ እንደሆኑ የሚያመላክት ዘረኛ ንግግር መናገራቸው ይታወሳል። ይህ ዘረኝነት የተጫነው ንግግራቸው አፍሪካ ኅብረትን ጨምሮ በርካታ የመብት ተሟጋቾችን አስቆጥቶ ነበር።

ባለፈው አርብ በብራስልስ ንግግር ያደረጉት የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ በቱኒዚያ መረጋጋት ካልመጣ ወደ አውሮፓ የሚገቡ ስደተኞች ቁጥር ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን እንደሚችል አስጠንቅቀው ነበር። ቱኒዚያ ከአይኤም ኤፍ ጋር ብድር ለማግኘት ያደረገችው ድርድር ውጤት ባለማስገኘቱ አሁን በአገሪቱ ከፍተኛ የምጣኔ ሃብት ምስቅልቅል መፈጠሩን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ዶናልድ ትራምፕ ከተከሰሰኩ በአሜሪካ ሞትና ውድመት ይከሰታል ሲሉ አስፈራሩ


አወዛጋቢው የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ከተከሰስኩ በአሜሪካ ሞትና ውድመት ይከሰታል ሲሉ ማስፈራራታቸው ተሰምቷል። ትራምፕ ከአንዲት ተዋናይት ጋር የነበራቸውን ግንኙነትን ለመደበቅ ገንዘብ ከፍለዋል በሚል ሊከሰሱ ይችላሉ ተብሏል።

የቀድሞ ፕሬዚዳንት እንደሚታሰሩ ከተነገረ ከአንድ ሳምንት ገደማ በኋላ በማህበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ባስተላለፉት መልእክት ደጋፊዎቻቸው ለተቃውሞ እና ለአመጽ እንዲወጡ መግለጻቸው ይታወሳል። እኤአ በ2024 በድጋሚ አሜሪካን በፕሬዚዳንትነት ለመምራት እንደሚወዳደሩ ያስታወቁት ዶናልድ ትራምፕ፣ የምታሰርና የምከሰስ ከሆነ በአሜሪካ ምድር ሞትና ውድመት ይከሰታል ሲሉ ዝተዋል ነው የተባለው።

ትራምፕ በተጨማሪም የማንሃተን አቃቤ ህግ ቢሮ እና ጉዳያቸውን የያዘው ዋና አቃቤ ህግ አልቪን ብራግ ላይ ተደጋጋሚ ዛቻዎችን ሲሰነዝሩ ነበረ ተብሏል። የትራምፕ አስተያየትን ተከትሎ በርካታ ደጋፊዎቻቸው ወደ ዐቃቤ ህግ አልቪን ብራግ 'እገልሃለሁ' የሚልን ጨምሮ በርካታ የማስፈራሪያ መልእክቶች እንዲሁም ነጭ ዱቄት የያዙ የፖስታ መልእክቶች መድረሳቸው ተሰምቷል።

የህግ አካላት በደብዳቤው ላይ ባደረጉት ማጣራት በዱቄቱ ውስጥ ጎጂ ነገር አለመገኘቱን አስታውቀዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሜሪካ ፖሊስ ከትራምፕ መከሰስ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለውን አለመረጋጋት ለመቆጣጠር በተጠንቀቅ ላይ መሆኑን ማስታወቁ የሚታወስ ነው፡፡

በዚህም በኒውዮርክ፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና ሎስ አንጀለስ ያለው የፖሊስ ኃይሎች ስምሪት



ዶናልድ ትራምፕ

መጠናከሩን ባለስልጣናት ገልጸዋል። ትራምፕ በቁጥጥር ስር የሚውሉ ከሆነ የማንሃታን አቃቤ ህግ ከአንዲት የወሲብ ፊልም ተዋናይት ጋር የነበራቸውን ግንኙነትና ተዋናይዋን ዝም ለማስባል ገንዘብ ከፍለዋታል የሚል ክስ ሊመሰርት ይችላል ተብሏል፡፡

ትራምፕ በተባለው የወንጀል ድርጊት የሚከሰሱ ከሆነ በአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዚዳንቶች ታሪክ በእንዲዚህ አይነት ቅሌት የተከሰሱ የመጀመሪያው መሪ እንደሚሆኑ አል ዐይን ዘግቧል፡፡


## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዢ መለያ ቁጥር ECC JB1/2015

የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ግዢ መፈጸም ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በጨረታው ለመወዳደር የሚፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት በጨረታው መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. በዘርፉ የተሰማሩና የታደሰ የንግድ የስራ ፍቃድ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
4. በዘርፉ ከሚመለከተው ፍቃድ ሰጪ አካል የእውቅና እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችሉ
5. በህዝብ አውቶቢሶች አራተኛና ከአራተኛ በላይ ወይም የህዝብ ሁለት መንጃ ፍቃድ ያለው፣
6. የተሽከርካሪው ሙሉ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልና አገር አቋራጭ አውቶቢስ 60 ሰው በተገቢው መያዝ የሚችል
7. ሁለት የመግቢያና የመውጫ በር ያለው ሆኖ መስኮቶቹ ሁሉ የሚከፈቱ መሆን አለበት
8. የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ያለውና ግብር የገበረ የመንገድ ትራንስፖርት ቦሎ ያለው
9. ተጫራቾች ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ እና እሁድ ሙሉ ቀን እና በዓላት ቀን ክፍያና ስራ የሌለ መሆኑን አውቆ የሚጫረት ሆኖ መ/ቤቱ ለስራ ከፈለገው የሚሰራ
10. የጨረታ ማስከበሪያ 10,000.00 (አስር ሺ) ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በንግድ ባንክ የተመሰከረለት (CPO) ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዞ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
11. ተጫራቾች ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቅዳሜ እስከ 6፡00 ሰዓት ጨምሮ በሚቆጠር 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለጨረታ ሰነዱ ብር 100.00 (አንድ መቶ) ብር በጥሬ ገንዘብ በመክፈል ሰነዱን ከጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት ከገቢ ሒሳቦች ቡድን መግዛት ይችላሉ፡፡
12. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ቴክኒካል እና ፋይናሻል ለየብቻ ከአንድ ኮፒ ጋር መስሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በጨረታው ቀን እስከ ጠዋቱ 4፡00 ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡፡
13. ጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚያኑ ዕለት 4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት 1ኛ ፎቅ የቢሮ ቁጥር 05 ጨረታው ይከፈታል አስራ አምስተኛው ቀን እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በቀጣዩ ቀን ጨረታው ይካሄዳል፡፡
14.ተጫራቾች በጨረታው ቀን የሚወዳደሩበት ተሽከርካሪ በአካል ወይም በቪዲዮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
15. አሸናፊው ድርጅት የሀገር አቋራጭ አውቶቢስ የማሽከርከር ፍቃድ ያለው ሾፌርና ረዳት ማቅረብ የሚችል
16. ለጨረታ የሚቀርበው የአውቶቢስ ደረጃ ነገር ግን በአንደኛ ደረጃም መወዳደር የሚችል ሲሆን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ ቢያንስ ሁለተኛ ደረጃ ሆኖ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡
17. ጨረታው ጋዜጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ በ4:00 ሰዓት ታሽጎ በዚያኑ ዕለት 4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት 1ኛ ፎቅ የቢሮ ቁጥር 05 ጨረታው ይከፈታል፡18.
18. ተጫራቾች በጨረታው ቀን የሚወዳደሩበትን ተሽከርካሪ ይዘው መቅረብ ይኖርበታል፡
19. ቅ/ጽ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታው ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻችን :-** በጅግጅጋ ጉምሩክ ጽ/ቱ ግዢና ፋይናንስ ቡድን 1ኛ ፎቅ የቢሮ ቁጥር 05

**መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 0915748790-0116733815**

**E-mail addreess Getachewtak1@gmail.com**

**የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**



## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ


በፍ/ባለመብት አቶ ባወቀ እንዳለ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ እነዳለ መላኩ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 95554 በ30/9/2013 ዓ.ም እና መ/ቁ 25740 የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ውስጥ የሚገኝ የቤ.ቁ 237 የተመዘገበውን ቤት በመለያ ቁጥር AA000100903846 የተመዘገበ ካርታ ያለው ስፋቱ 414 ካ/ሜ የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 1,089,040(አንድ ሚሊዬን ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ አርባ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

# ስፖርት



# ኢትዮ ኤሌክትሪክን ከመውረድ ለመታደግ የተወሰዱ ርምጃዎች

**አስማማው ግዛው**

ስለኢትዮጵያ እግር ኳስ ክለቦች ሲነሳ የማንዘነጋው አንድ ክለብ አለ። ክለቡ ታሪካዊ ነው። ከቅዱስ ጊዮርጊስና ሀዋሳ ከነማ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ እንደ አዲስ ከ1990 ጀምሮ ሲካሄድ ሁለት ጊዜ ቻምፒዮን ከሆኑ ጥቂት ክለቦች አንዱ ነው። የቀድሞው መብራት ኃይል የአሁኑ ኢትዮ ኤሌክትሪክ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ባለውለታ ከሆኑ ክለቦች አንዱ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህ ክለብ በቀደሙት ዓመታት ታሪኩ በርካታ ተጫዋቾችን ለአገር በማፍራት ይታወቃል።

ምስረታው ከታዳጊዎች የሚጀምር ሲሆን አንዋር ትንሹና ኤሊያስ ጀዋርን የመሳሰሉ ታሪካዊ ተጫዋቾችን በማፍራት ተጠቃሽ ነው። በክለቡ ተጫውተው ካለፉ ታላላቅ ተጫዋቾች መካከልም ዮርዳኖስ አባይ፣ ሙሉዓለም ጥላሁን፣ ረዲ አብረሃና በረከት ተሰማን ከብዙ በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል። ለበርካታ ክለቦችና ብሔራዊ ቡድን በርካታ ተጫዋቾችን በማበርከትም በወርቃማ ዘመኑ «የኢትዮጵያው ላማስያ» እስከ መባልም ደርሷል።

ከአዲስ አበባ ክለቦች መካከል አንዱ ሆኖ በ1953 ዓ.ም ሲመሰረት፣ የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ ለሶስት ጊዜያት ከፍ ማድረግ ችሏል። ፕሪሚየር ሊጉን ጨምሮም በታሪኩ 13 ዋንጫዎችን በማንሳት ትልቅ ዝናና ስም ገንብተል። በአፍሪካ ደረጃም በካፍ ቻምፒየንስ ሊግና ኮንፌዴሬሽን ውድድሮች ደጋግሞ መሳተፍ ችሏል።

ይህ ታሪካዊ ክለብ ለዓመታት ብርቱ ተፎካካሪ ከሆነበት ፕሪሚየር ሊግ ወርዶ ከዓመታት ቆይታ በኋላ ዘንድሮ መመለስ ቢችልም የስሙንና የታሪኩን ግዝፈት ያህል በጠንካራ ተፎካካሪነት ለመዝለቅ እየተቸገረ ይገኛል። ከከፍተኛ ሊግ ባደገ በዓመቱ ተመልሶ እንዳይወርድም አሁን እየተጓዘበት ያለው መንገድ ለደጋፊዎቹ የሚያሰጋ ነው። ክለቡ አሁን በቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ በወራጅ ቀጠና ውስጥ ይገኛል። አስራ ስድስት ጨዋታዎችን አድርጎ ማሸነፍ የቻለው አንዱን ብቻ ነው። 26 ግቦች ሲቆጠርበት ማስቆጠር የቻለው 16 ግቦችን ነው። በ8 ነጥብና በ10 የግብ እዳ 15ኛ ደረጃን በመያዝም የመውረድ ስጋት ተጋርጦበታል።

ከዚህ ስጋቱ ለመውጣት ግን አሁን ወደራሱ የሚመለከትበት መልካም አጋጣሚ ተፈጥሯል። የፕሪሚየር ሊጉ የመጫወቻ ሜዳ በዝናብ ምክንያት መቋራረጡና ብሔራዊ ቡድኑ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ምክንያት ተቋርጧል። ይሄንንም አጋጣሚ ክለቡ ባገኘው ፋታ እራሱን አርሞ ከመውረድ ለመዳን እንደሚጠቀምበት ጠቁሟል።

ክለቡ በጥር የዝውውር መስኮት ያስፈረማቸውን ተጫዋቾችን በመጨመር ለሁለተኛው ዙር የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታ ጠንካራ ዝግጅት አድርጎ በሊጉ ለመቆየት በመስራት ላይ መሆኑን አስታውቋል። በዝውውር መስኮቱ እራሱን መፈተሹንና ብቃታቸው የወረደ ሰባት ተጨዋቾችን አሰናብቶ ስድስት አዳዲስ ተጫዋች ክለቡን እንዲቀላቀሉ ማድረጉን ጠቁሟል። ክለቡ ከከፍተኛ ሊግ ወደ ፕሪሚየር ሊግ ካሳደገው አሰልጣኝ ክፍሌ ቦልተና ጋር በውጤት መጥፋት ምክንያት ከተለያየ በኋላ አሰልጣኝ ገዛኸኝ ከተማን በዋና አሰልጣኝነት መቅጠሩ ይታወሳል። በአዲሱ አሰልጣኝ ስርም የቀጠለው የውጤት መጥፋት በቀጣይ ሁለተኛ ዙር ውድድር ለመቅረፍና በሊጉ ለመቆየት ከአሰልጣኙና ተጫዋቾች ጋር መግባባቱን ጠቅሷል።

የኢትዮ ኤሌክትሪክ ስፖርት ክለብ ስራ አስኪያጅ አቶ ሲሳይ ለማ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፣ ከወራጅ ቀጠናው ለመውጣትና በፕሪሚየር ሊጉ ለመቆየት ከተጨዋቾችና ከአሰልጣኝ ቡድኑ ጋር ውይይት ተደርጎ መግባባት ተችሏል። የክለቡ አመራር ከተጫዋቾቹ ጋር ውይይቶችን አድርጎ ቅሬታዎችን እንደግብዓት መወሰዱን የጠቆሙት ስራ አስኪያጁ፣ በእያንዳንዱ ጨዋታ ላይ ግምገማ እየተደረገ እንደሆነም ገልጸዋል። ይህ አሁንም ተጠናክሮ የሚቀጥል



ኢትዮ ኤሌክትሪክ ለሁለተኛው ዙር ፕሪሚየር ሊግ ጠንካራ ዝግጅት አድርጎ በሊጉ ለመቆየት አስቧል፣

ሲሆን ቀሪ 14 ጨዋታዎች እንደ ጥሎ ማለፍ ጨዋታዎች እንደሚመለከቱም ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል። በቀጣይም ችግሩን ለመፍታት ከደጋፊ ማህበሩ ጋርም ውይይት እንደሚኖራቸው ጠቁመዋል። በተጨማሪም ከፌዴሬሽንና ከዳኞች ማህበር ጋር ያሉትን ችግሮች ለማቃለል መሰል ውይይት እንደሚያደርጉ አስረድተዋል።

ክለቡ ኢፍታዊ በሆኑ የዳኝነት ክፍተቶች ምክንያት ውጤት እንዳያጣ ብቃት ያላቸው ዳኞች እንዲመደቡ ለማድረግ እንደሚታገል የገለፁት ስራ አስኪያጁ፣ በአጠቃላይ በእያንዳንዱ ጨዋታ የክለቡ አመራር ድጋፍና ክትትል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ኢትዮ ኤሌክትሪክ በሚታወቅበት ታዳጊዎችን የማፍራት ባህል እንዳይቀጥል የሌሎች ክለቦች ውጤትን ትኩረት ያደረገ የአስተዳደር ስርዓት መከተሉ ተጎጂ እንዳደረገው አቶ ሲሳይ ያምናሉ። ለዚህም የውጭ ተጫዋቾችን ማስፈረም ለታዳጊዎች የሚሰጠውን ትኩረት መቀነሱንና ክለቡንም ተጎጂ ማድረጉን ያብራራሉ። እነዚህና ሌሎች መሰል ነገሮችም ለክለቡ ውጤት ማጣት ተጠቃሽ መሆናቸውን ያስቀምጣሉ። ክለቡ አሁንም ታዳጊዎችን የማፍራት ባህሉን ጠብቆ ለመጓዝ ከግብ ጠባቂ ጀምሮ ወደ ዋናው ቡድን ወጣቶችን ለማሳደግ ጥረት እያደረገ ይገኛል። በዚህም ክለቡ የውጭ ተጫዋቾችን ከማምጣት ይልቅ ቅድሚያ ለሀገር ውስጥ ተጫዋቾች እንደሚሰጥ ጠቁመዋል። «ክለቡ የቀድሞ ባህሉንና ፍልስፍናውን በማስቀጠል በሊጉ መቆየት ብቻ ሳይሆን ውጤታማ ለመሆን መስራት ይጠበቅብናል» ሲሉም ተናግሯል።

የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ገዛኸኝ ከተማ በበኩሉ፣ ቡድኑን ለመታደግ ያስፈረሟቸውን አዳዲስ ተጫዋቾች በማካተት ለሁለተኛ ዙር ዝግጅት በማድረግ ውጤት እንደሚያስመዘግቡም ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል። አሰልጣኙ ክለቡን ከወራጅ ቀጠናው ለማውጣት እየሰሩ መሆናቸውን ገልጸው፣ ክለቡ ታሪካዊ በመሆኑ በሚገባው ቦታ መቀመጥ እንደሚገባውም ይናገራሉ። ተጫዋቾቹ በተነሳሽነት ረገድ ያለውን ጫና ስለሚያውቁ በስነልቦና ረገድ በባለሙያ የተደገፈ ዝግጅትን በማድረግ ላይ እንደሚገኙም አክለዋል። በክለቡ ተጫዋቾች ላይ የሚታየውን መነሳሳት ተጠቅመውም ክለቡን ከመውረድ ለመታደግ እየሰሩ ይገኛሉ።



ዕለተ ሰንበት

ለልጆች

# መስራት ያስከብራል

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ልጆች ዛሬ ስራን ሳይንቅ ሰርቶ ራሱን የሚያስተምረውን ታዳጊ ላስተዋውቃችሁ ወደድኩ።

ጀልቀባ አበራ ይባላል፤ በአምቦ ከተማ የሚኖር የ14 ዓመት ታዳጊ ሲሆን የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ከዕለታት በአንዱ ቀን ለምን ስራ ሰርቼ ራስን አልደግፍም የሚል ሃሳብ ወደ አዕምሮው ይመጣል። ከዚያም በአካባቢው ከሚኖር ሌላ ታዳጊ የመፋቂያ እንጨት ስራ እንዴት እንደሚሰራ ለተወሰኑ ቀናት ልምድ ለመውሰድ አብሮ እየሰራ ከተማረ በኋላ ራሱን ችሎ መስራት እንደሚችል እርግጠኛ ሲሆን ስራውን ያለጓደኛው እርዳታ ብቻውን መስራት ጀመረ። ስራውን በደንብ ከለመደ በኋላ ገቢ ማግኘት ሲጀምር ሃያ ጫጩት ዶሮዎች ገዝቶ ማርባት ጀመረ፤ አሁን ላይ የገዛቸው ዶሮዎች አድገው ትልልቅ ሆነውለታል።

ይህ ታዳጊ በአምቦ ከተማ ውስጥ የጥርስ መፋቂያ በመሸጥ ለራሱ ስራ ፈጥሮ የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ሰርቶ በሚያገኘው ገቢ በመሸፈን ቤተሰቦቹ ያለባቸውን የኑሮ ጫና ለማገዝ የሚሞክር ታታሪ ታዳጊ ነው። የሚሸጠውን የጥርስ መፋቂያ እንጨት ጉደር ከምትባል ቦታ በመሄድ ካመጣ በኋላ ቆራርጦ በማስተካከል ለገበያ ያቀርባል። ልጆች ጉደር ከአምቦ ከተማ ራቅ ብሎ የሚገኝ ቦታ ነው። ታዲያ ጀልቀባ የመፋቂያ እንጨቱን ለማምጣት ከአምቦ ጀምሮ ጉደር ድረስ የሚሄደው በእግር ጉዞ ነው። እንጨቱን ይዞ ሲመለስም የሚጓዘው በእግሩ ነው። የመፋቂያ እንጨቱን ጉደር ድረስ ሄዶ ካመጣ በኋላ በሚያማምር ቅርፅ ቆራርጦ በማዘጋጀት ለገበያ ዝግጁ ያደርጋቸዋል። ከዚያ በኋላ ትምህርት የሚማሩት በፈረቃ በመሆኑ ትምህርት ቤት የሚሄደው ጠዋት ከሆነ ሲመለስ ከሰዓት በኋላ የሰራቸውን የጥርስ መፋቂያዎች ይዞ ወደሚሸጥበት ቦታ ይሄዳል። ትምህርት ቤት የሚሄደው ከሰዓት በኋላ ከሆነ ደግሞ



ተማሪ ጀልቀባ አበራ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ እጅ የእውቅና የምስክር ወረቀት ሲቀበል፣

ጠዋት ስራውን ሲሰራ ይቆይና ሰዓቱ ሲደርስ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል።

ጀልቀባ ይህንን ስራ የጀመረው በሀምሳ ብር ብቻ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ በቀን ከሰማንያ እስከ መቶ ብር ያገኛል። ቤተሰቦቹ ሰባት ልጆችን ስለሚያሳድጉ ጀልቀባን በሚፈልገው መጠን ለመደገፍና የሚፈልገውን አሟልተው ለማሳደግ አቅም የላቸውም፤ በመሆኑም ሰርቶ በሚያገኘውን ብር ሳሙና የትምህት ቤት ዩኒፎርምና የተለያዩ ልብሶችና የሚያስፈልጉትን ይገዛል። ደብተር፣ እስክሪብቶና እርሳስም ቢሆን የሚገዛው እራሱ ሰርቶ በሚያገኘው ገቢ ነው። ልጆችዬ ጀልቀባ ታታሪነቱ በስራ ብቻ እንዳይመስላችሁ በትምህርቱም ቢሆን ጎበዝ ተማሪ ነው።

የሚሰራው ስራ ከትምህርቱ ጋር እንዳይጋጭበት የስራና የትምህርት ሰዓቱን ከፋፍሎ ይጠቀማል፤ ትምህርት ባለበት ሰዓት ወደ ትምህር ቤት ይሄዳል ከትምህርት ቤት ሲመለስ ደግሞ ስራውን ይሰራል። ማጥናት ባለበት ሰዓትም ትምህርቱን በአግባቡ ያነባል። ወደፊት በትምህርቱ ጠንክሮ ጥሩ ውጤት በማምጣትና ጎበዝ ሰራተኛ በመሆን በጉደር እና በአምቦ ከተማ ላይ የራሱን ትልልቅ ህንፃዎች ገንብቶ ስራውን እየሰራ መኖር ይፈልጋል። ይህንን ለማሳካትም ካሁኑ የስራ ባህሉን እያሳደገና በርትቶ እየተማረ ይገኛል።

ልጆች ጠንክሮ መስራት የራስን ችግር ከማሸነፍና የስራ ባህልን ከማዳበር ባሻገር በተለያዩ ቦታዎች ላይ ክብርና ሞገስን እንደሚያጎናፅፉ ታውቃላችሁ አይደል? ታዳጊ ጀልቀባም ለስራ የሰጠው ክብር እና ስራን ሳይንቅ ዝቅ ብሎ በመስራቱ ክብር ተሰጥቶታል። ባሳየው የስራ ትጋትና ማንንም ሳያስቸግር የራሱን ስራ ፈጥሮ በመስራቱ በርካታ ታዳሚዎች በተገኙበት መድረክ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ እጅ የእውቅና የምስክር ወረቀት ተቀብሏል።

ታዳጊ ጀልቀባ ልጆች መስራት አለባቸው ስራ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፤ ስለዚህ ልጆች አቅማቸው የሚችለውን በመስራት እና ቤተሰቦቻቸውን በማገዝ ከልጅነታቸው ጀምሮ የስራን ባህል ማዳበር አለባቸው በማለት መልዕክቱን ያስተላልፋል። ልጆች እናንተም የስራ ባህልን ከልጅነታችሁ ጀምሮ ማዳበርና ስራን መስራት ልትለማመዱ ይገባል። ነገር ግን የግድ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራ መስራት አለብኝ ብላችሁ ቤተሰቦቻችሁን ማስቸገር የለባችሁም ቤት ውስጥ ቤተሰቦቻችሁን በማገዝም ስራን መለማመድ ትችላላችሁ። ለዛሬ በዚሁ ላብቃ ሳምንት በሌላ ፅሁፍ እስከንገናኝ ድረስ መልካም የትምህርት ሳምንት ይሁንላችሁ።